# እንቅልፍ ፡ ለምኔ ።

ሦስተኛ ፡ እትም ፤

ከብላቴን ፡ ጌታ ፡ ማኅተመ ፡ ሥላሴ ፡ ወ ፡ መ ፡
ተዘጋጀ ።

ተኅትመ ፡ ዝንቱ ፡ መጽሐፍ ፡ በ፴ወ፮ ፡ ዘመነ ፡ መንግሥቱ ፡
ለቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ዘኢትዮጵያ ።

አዲስ ፡ አበባ ፡ ሐምሌ ፡ ፲፮ ቀን ፡ ፲፱፻፷፮ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ም ፡

በአርቲስቲክ ፡ ማ ተ ሚ ያ ፡ ቤ ት ፡ ታ ተ መ ።

አጠቃላይ አስመጪ ☆
20 17 38
P. O. Box 16171
53 03 26
Abeba
Mebadere Yitag...
Importer

398
ማ
1ኛ:ቅ.

ያለደራሲው ፡ ፈቃድ ፡ መልሶ ፡ ማተም ፡
ክልክል ፡ ነው ።

**All Right reserved**



ግርማዊ ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡
ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ዘኢትዮጵያ ።

# ባልና ፡ ሚስትን ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ እንዳታለላቸው ።

ባልና ፡ ሚስት ፡ ሆነው ፡ ይኖሩ ፡ የነበሩ ፡ ሁለት ፡ ሰዎች ፡ ባንድ ፡ ጊዜ ፡
ሞቱ ፡ ይባላል ። የወለዱትም ፡ ልጅ ፡ አንዲት ፡ ሴት ፡ ልጅ ፡ ብቻ ፡ ስት
ሆን ፡ እሷውም ፡ በጣም ፡ ቂልነትን ፡ የምታበዛ ፡ ነበረች ። ትዳር ፡ መያ
ዝም ፡ ስለማይቀር ፡ ባል ፡ አግብታ ፡ ስትኖር ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ እናትና ፡
አባቷ ፡ ከሞቱ ፡ በኋላ ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ቄይቶ ፡ ባሏ ፡ ወደ ፡ መንገድ ፡ ሲሄድ፡
አንድ ፡ አታላይ ፡ ሰው ፡ ተጠባብቆ ፡ መጣና ፡ ቤቶች ፡ እንደ ፡ ምን ፡ ዋላ
ችሁ ፡ አለ ። ሴቲቱም ፡ ብቅ ፡ አለችና ፡ እግዚአብሔር ፡ ይመስገን ፡ ብላ ፡
ሰላምታ ፡ ከሰጠችው ፡ በኋላ ፡ ወንድሜ ፡ ከወዴት ፡ መጥተሃል ፡ አለችው።
ሰውዮውም ፡ እናትሽና ፡ አባትሽ ፡ ልከውኝ ፡ ነው ፡ አላት ። ምን ፡ ብለው ፡
ላኩህ ፡ ለጤናቸውስ ፡ ደኅና ፡ ናቸውን ፡ ብላ ፡ ብትጠይቀው ፡ ደኅንነቱንስ፡
ደኅና ፡ ናቸው ፡ ብቻ ፡ ስለ ፡ ተራቆቱ ፡ ከልጃችን ፡ ዘንድ ፡ ልብስ ፡ አምጣ
ልን ፡ ብለው ፡ ነው ፡ የላኩኝ ፡ አላት ።

ይህንንም ፡ እንደ ፡ ነገራት ፡ አዩ ፡ ጉድ ፡ ተራቍተውብኛላ ፡ በል ፡ ና ፡
ብላ ፡ ከቤት ፡ አስገብታ ፡ ምሳውን ፡ አብልታ ፡ መጠጥ ፡ አጠጥታ ፡ የባሏን ፡
ሰናፊል ፡ እጀ ፡ ጠባብ ፡ በሰንበት ፡ ቀን ፡ የሚለብሰውን ፡ ኩታውን ፡ ጃኖውንና፡



አዩ ፡ ጉድ ፡ ተራቍተውብ
ኛላ ፡ በል ፡ ና ፡ ብላ ፡ ከቤት ፡
አስገብታ ፡ በስልቻ ፡ ከታ ፡
ሰጠችው ።

ድጉን ፡ ከተቀመጠበት ፡ ማጀት ፡ ከጋን ፡ ውስጥ ፡ አውጥታ ፡ ይኸንን ፡ ላባቱ ፡
ስጥልኝ ፤ ደግሞ ፡ የርሷን ፡ ቀሚስና ፡ ኩታ ፡ መቀነትና ፡ የራስ ፡ ማሰሪያ ፡



ለናቴ ፡ ስጥልኝ ፤ ሰላምታም ፡ እናንተ ፡ እንደምንድናችሁ ፡ እኔ ፡ ጤናዬን ፡
ደኅና ፡ ነኝ ፡ ብለህ ፡ ንገርልኝ ፡ ልብሱንም ፡ አሁን ፡ ቶሎ ፡ ብለህ ፡ አድርስ



እረ ፡ ለነገሩ ፡ ማነው ፡ ስምህ ፡
ስትል ፡ ጠየቀችው ።

ላቸው ፡ ብላ ፡ በስልቻ ፡ ከታ ፡ ሰጠችው ። ወዲያው ፡ እረ ፡ ለነገሩ ፡ ማነው ፡
ስምህ ፡ ስትል ፡ ጠየቀችው ። እሱም ፡ ስሜ ፡ አታለለኝ ፡ ነው ፡ ብሏት ፡ ሰታ
ውን ፡ ይዞ ፡ ሄደ ። ጥቂት ፡ ቄይቶ ፡ እንዳጋጣሚ ፡ ባሏ ፡ ከሄደበት ፡ መንገድ ፡
መጣ ፡ ወዲያው ፡ ገና ፡ ሳያርፍ ፡ አንቱዬ ፡ ዛሬ ፡ እናቴና ፡ አባቴ ፡ ልብስ ፡ አል
ቆብናል ፡ ላኩልን ፡ ብለው ፡ መልክተኛ ፡ ስለ ፡ ላኩ ፡ የርስዎን ፡ የክት ፡ ልብስ ፡
ሰናፊልዎንና ፡ ድግዎን ፡ እጀ ፡ ጠባብዎንና ፡ ኩታዎን ፡ እንዲሁም ፡ ጃኖዎን ፡
ላባቴ ፡ የኔን ፡ ቀሚስና ፡ ኩታ ፡ መቀነትና ፡ የራስ ፡ ማሰሪያ ፡ ለናቴ ፡ ሰደድኩ
ላቸው ። ሰላምታም ፡ እናንተ ፡ እንዴት ፡ ናችሁ ፡ እኛ ፡ ደኅና ፡ ነን ፡ ብለው ፡
ልከው ፡ ነበር ፡ አለችው ።

እሱም ፡ ተናደደና ፡ አዬ ፡ ጉድ ፡ ከመቼ ፡ ወዲህ ፡ ነው ፡ የሞተ ፡ ሰው ፡
ልብስ ፡ የሚፈልገው ፡ እንዲያው ፡ ሲያታልልሽ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ለመሆኑ ፡
በየት ፡ በኩል ፡ ነው ፡ የሄደው ፡ አሳዩኝ ፡ አላት ። እርስዋም ፡ ያውልዎ ፡
በዚያ ፡ በኩል ፡ ነው ፡ አለችው ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ሦንጋ ፡ ፈረሱን ፡ ጭኖ ፡
ሲጋልብ ፡ አታላዩ ፡ ሰው ፡ እንደሚከተለው ፡ ጠርጥሮ ፡ ኖሮ ፡ ያንን ፡ ልብስ ፡
ከነስልቻው ፡ እቍጥቋጠ ፡ ሥር ፡ ደብቆ ፡ ከዛፉ ፡ ሥር ፡ ቍጭ ፡ ብሎ ፡
ቈየው ።

ፈረሰኛውም ፡ እንደ ፡ ደረሰ ፡ ወንድሜ ፡ በዚህ ፡ መንገድ ፡ የተቋጠረ ፡
ስልቻ ፡ የያዘ ፡ ሰው ፡ ሲሄድ ፡ አላየህምን ፡ አለው ። እሱም ፡ በዚህ ፡ ሸለቆ ፡ ወደ፡

# አንድ ፡ በሬ ፡ ስለ ፡ ነበራቸው ፡ ቂሎች ፡ ባልና ፡ ሚስት ።

ከዕለታት ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ እነዚህ ፡ ሰዎች ፡ ኑሯቸውን ፡ ሲወያዩ ፡ ሴትዮዋ ፡ ለባሏ ፡ ችግርና ፡ ረኃብ ፡ ጸናብን ፡ ፎኸንን ፡ በሬያችንን ፡ አርደን ፡ እንብላው ፡ ብላ ፡ አሳሰበችው ። ባሏም ፡ እውነትሽ ፡ ነው ፡ እንረደው ፡ አላት። ሁለቱም ፡ በሐሳቡ ፡ ስለ ፡ ተስማሙ ፡ በሬውን ፡ ከዛፍ ፡ ሥር ፡ አርደው ፡ ብልት ፡ ሲያወጡ ፡ አሞራ ፡ እየመጣ ፡ አንዳንዱን ፡ ሙዳ ፡ እየያዘው ፡ ይሄድ ፡ ገመረ ፤ በዚህ ፡ ጊዜ ፡ እሱ ፡ የወሰደከው ፡ ሥጋ ፡ የብር ፡ ነው ፡ ማለት ፡ ያዙ ። ደግሞ ፡ ጭልፊቶች ፡ ሥጋው ፡ ስለ ፡ ጣማቸው ፡ እየተመላለሱ ፡ በጥፊ ፡ እያነጐዱ ፡ ቅንጥብጣቢ ፡ ሲነጥቁ ፡ እኛ ፡ ነግረናል ፡ አሁን ፡ የወሰዳችሁት ፡ የብር ፡ ነው ፡ ዐውቃችሁ ፡ ግቡበት ፤ ይምሩናል ፡ ብላችሁ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ አታስቡ ፡ በማለት ፡ ሲወተውቱ ፡ ከቈዩ ፡ በኋላ ፡ ቈዳውን ፡ ገፈው ፡ ሲያበቁ ፡ የተረፈውን ፡ ሥጋ ፡ በጋን ፡ ቀቅለው ፡ በመግላሊት ፡ ከድነው ፡ እንግዲህ ፡ ስንበላ ፡ እጥርሳችን ፡ የሚገባውን ፡ ለመጐርጐሪያ ፡ ስንደዶ ፡ አጭደን ፡ እናምጣ ፡ ብለው ፡ የቤታቸውን ፡ ጭራሮ ፡ መዝጊያ ፡ መለስ ፡ አድርገው ፡ ማጭድና ፡ መጫኛ ፡ ይዘው ፡ ሁለቱም ፡ ተያይዘው ፡ ከቤት ፡ ወጡ ። ወዲያው ፡ በዚያው ፡ መንገድ ፡ ባጠገባቸው ፡ ብዙ ፡ ወታደሮች ፡ ተፍ ፡ ተፍ ፡ እያሉ ፡ መጡ ።

በዚህ ፡ ጊዜ ፡ እናንተ ፡ ጐበዞች ፡ ስሟችሁ ፡ በዚህ ፡ በምትሄዱበት ፡ መንገድ ፡ አጠገብ ፡ በጭራሮ ፡ መዝጊያ ፡ የተዘጋ ፡ ቤት ፡ አለና ፡ እኛ ፡ በሬያችንን ፡ አርደን ፡ ሥጋውን ፡ በጋን ፡ ቀቅለን ፡ በመግላሊት ፡ ከድነን ፡ ከወፍጮም ፡ ላይ ፡ ዳቦ ፡ በሌማት ፡ አስቀምጠን ፡ ለጥርሳችን ፡ መጐርጐሪያ ፡ ስንደዶ ፡ ለማጨድ ፡ መጥተናል ፤ በዚያ ፡ ስታልፉ ፡ እንዳትነኩብን ፡ ብለው ፡ ነገሯቸው ። መንገደኞቹም ፡ ይህንን ፡ በሰሙ ፡ ጊዜ ፡ ገሥግሠው ፡ ሄደው ፡ ያንን ፡ የጭራሮ ፡ መዝጊያ ፡ ከፍተው ፡ ሥጋውን ፡ እደቅ ፡ ላይ ፡ እያወጡ ፡ በልተው ፡ ከጠገቡ ፡ በኋላ ፡ ፀጥንቱን ፡ መልሰው ፡ እጋኑ ፡ ውስጥ ፡ ጨምረው ፡ መግላሊቱን ፡ እንደ ፡ ነበረ ፡ ከደኑት ። በሌማት ፡ የነበረውንም ፡ ዳቦ ፡ እየተከፋፈሉ ፡ በጭብጦ ፡ መያዣቸው ፡ ከቋጠሩ ፡ በኋላ ፡ ጭራሮ ፡ መዝጊያውን ፡ መለስ ፡ አድርገው ፡ ተነሥተው ፡ መንገዳቸውን ፡ ቀጠሉ ።



ወታደሮቹም ፡ በዝብዘው ፡ ከሄዱ ፡ በኋላ ፡ ባልና ፡ ሚስቱ ፡ ስንደዱቸውን ፡ ተሸክመው ፡ መጡና ፡ ቤታቸውን ፡ ከፍተው ፡ ቢገቡ ፡ መግላሊቱ ፡ ተንከርፍፎ ፡ ዝንቡ ፡ እቤት ፡ ባለው ፡ ዕቃ ፡ ላይ ፡ በጋኑም ፡ በዋዲያቱም ፡ በአፍላሉም ፡ በበገፈጁም ፡ ዳቦ ፡ በነበረበት ፡ ሌማትም ፡ እቤት ፡ ባለው ፡ ደጃፍ ፡ በመለሰውና ፡ ማጀት ፡ በጐረሠው ፡ በማናቸውም ፡ ላይ ፡ ሰፍሮበት ፡ አዩ ። መግላሊቱን ፡ ከጋኑ ፡ ቢያነሡት ፡ ዝንቡ ፡ እው ፡ እያለ ፡ ከውስጡ ፡ ይወጣ ፡ ገመር ። እጃቸውንም ፡ አግብተው ፡ ቢዳብሱት ፡ አጥንቱ ፡ ብቻ ፡ ቃጕሮ ፡ ሥጋው ፡ ተበልቶ ፡ አገኙት ። ሥጋችንን ፡ የበላብን ፡ ይኸ ፡ ዝንብ ፡ አይደለምን ፡ እንክሰሰው ፡ ብለው ፡ ተነሥተው ፡ ወደ ፡ ዳኛ ፡ ሄደው ፡ አቤት ፡ አቤት ፡ እያሉ ፡ ጮኹ ። ዳኛውም ፡ ምነው ፡ ምን ፡ ሆናችሁ ፡ ምንስ ፡ ተበድላችሁ ፡ ነው ፡ በማለት ፡ ጠየቃቸው ። እነሱም ፡ ጌታችን ፡ ሆይ ፡ እግዚአብሔር ፡ ያሳይዎ ፡ መልአኩ ፡ ይንገርዎ ፡ በሬያችንን ፡ አርደን ፡ ሥጋውን ፡ በጋን ፡ ቀቅለን ፡ በመግላሊት ፡ ከድነን ፡ ዳቧችንንም ፡ በሌማት ፡ አኑረን ፡ ቤታችንን ፡ ዘግተን ፡ ለጥርሳችን ፡ መጐርጐሪያ ፡ ስንደዶ ፡ ለማጨድ ፡ ሄደን ፡ ተመልሰን ፡ ብንመጣ ፡ ዝንብ ፡ ዐጥንቱ ፡ ብቻ ፡ እስኪቀር ፡ ሥጋውን ፡ በልቶ ፡ ዳቧችንን ፡ ጨርሶ ፡ አገኘነው ። የንቀቱ ፡ ንቀት ፡ የድፍረቱ ፡ ድፍረት ፡ ከዚህ ፡ ሁሉ ፡ ጥፋት ፡ በኋላ ፡ ከቤታችን ፡ ዕቃ ፡ ላይ ፡ ሰፍሮ ፡ ቈየን ። እኛንም ፡ አይቶ ፡ ትንሽ ፡ እንኳ ፡ ደንገጥ ፡ አላለም ። ዝም ፡ ብሎ ፡ የተረፈውን ፡ ይበላል ፡ አሉት ። ዳኛውም ፡ የዚህ ፡ ፍርድ ፡ አስቸጋሪ ፡ አይደለም ፡ ሄዳችሁ ፡ ያለውን ፡ ዝንብ ፡ ሁሉ ፡ ፍጁት ፡ በገዛ ፡ ቤታችሁና ፡ በገዛ ፡ ሥጋችሁ ፡ ዝም ፡ በሉ ፡ አልልም ፡ አላቸው ። እነሱም ፡ ይህንን ፡ ፍርድ ፡ ተቀብለው ፡ እጅ ፡ ነሥተው ፡ ተመለሱ ።

ከቤታቸውም ፡ እንደ ፡ ደረሱ ፡ ባለቤቱ ፡ ፈጥኖ ፡ ቈመጡን ፡ አንሥቶ ፡ ዝንብ ፡ ለመግደል ፡ ሲሰነዝር ፡ ጋኑን ፡ ከነመግላሊቱ ፡ ብትንትን ፡ አደረገው ። ደግሞ ፡ ከዋዲያቱ ፡ ላይ ፡ ያረፈውን ፡ ሊገድል ፡ ሽመሉን ፡ ቢያወዘገዝገው ፡ ዋዲያቱን ፡ ጣባውን ፡ ጕልቻውንም ፡ ባንድ ፡ ጊዜ ፡ እንክትክት ፡ አደረገው ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ እያ ፡ ዝንጀሮ ፡ ጐንበስ ፡ ጐንበስ ፡ ሲል ፡ መጣና ፡ ወይዘሮ ፡ ጦጢት ፡ ምን ፡ ሆነሽ ፡ ታሰርሽ ፡ ምነው ፡ ምን ፡ አገኘሽ ፡ አላት ። እበክህን ፡ ወንድሜ ፡ የናትና ፡ ያበቴን ፡ ተዝካር ፡ ብዬ ፡ ጠጪ ፡ ቢሉኝ ፡



እቢም ፡ የእናቴ ፡ ቀሚስ ፡ አመላከፈኝ ፡ አለችና ፡ ሁለተኛ ፡ ለመዝለል ፡ ሞከረች።

አልበላም ፡ አልጠጣም ፡ ብዬ ፡ ነዋ ! አለችው ። ታዲያ ፡ ምን ፡ ቸገረሽ ፡ አትበዪም ፡ አትጠጪም ፡ ነበር ! ፡ ቢላት ፡ እኔ ፡ ብቻዬን ፡ አላልቅ ፡ አለኛ ፡ አለችው ። እንግዲያው ፡ እኔ ፡ እበላልሻለሁ ፡ እጠጣልሻለሁ ፡ እሰሪኝ ፡ አላት ። ደግ ፡ መልካም ፡ በል ፡ እኔን ፡ ፍታኝና ፡ ልሰርህ ፡ ስትል ፡ መለሰችለት ። ፈታትና ፡ እሱን ፡ ከዚያ ፡ ግንድ ፡ ጋራ ፡ የፈጥኝ ፡ ጠፍራ ፡ እንግዲህ ፡ መጥተው ፡ ሲጠይቁህ ፡ እበላለሁ ፡ እጠጣለሁ ፡ በል ፡ ብላ ፡ አስጠነቀቀችው ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ከዛፉ ፡ ላይ ፡ ወጥታ ፡ ቍጭ ፡ አለች ።

እነዚያም ፡ ሰዎች ፡ ፍልጣቸውን ፡ አዘጋጅተው ፡ ተሸክመው ፡ ቢመጡ ፡ በጦጣዋ ፡ ቦታ ፡ ዝንጀሮ ፡ ተተክቶ ፡ አገኙት ። አንተ ፡ ምን ፡ ታደርጋለህ ፡ ቢሉት ፡ እንኩዬ ፡ ጦጢት ፡ አልበላም ፡ አልጠጣም ፡ ብዬ ፡ ነው ፡ የታሰርኩት ፡ ብትለኝ ፡ እኔ ፡ እበላልሻለሁ ፡ እጠጣልሻለሁ ፡ ስላልኳት ፡ አስራኝ ፡ ሄደች ፡ አላቸው ። እረ ፡ የታበክንስ ፡ ብለው ፡ በዚያ ፡ በደሬ ፡ ፍልጥ ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ቢያቀምሱት ፡ እበላለሁ ፡ እጠጣለሁ ፡ እያለ ፡ ይለፈልፍ ፡ ዠመር ። እሷም ፡ ከንዱ ፡ ቅርንጫፍ ፡ ወደንዱ ፡ ቅርንጫፍ ፡ እየዘለለች ፡ የጦጣ ፡ ብልጣብልጥ ፡ የዝንጅሮ ፡ ቅልጣቅልጥ ፡ ተው ፡ በለው ፡ በደሬ ፡ ፍልጥ ፡ እያለች ፡ ሥጋው ፡ አልቆ ፡ ዐጥንቱ ፡ እስኪታይ ፡ ድረስ ፡ አስደበደበችው ።





እንኩዬ ፡ ጦጢት ፡ አልበላም ፡ አልጠጣም ፡ ብዬ ፡ ነው ፡ የታሰርኩት ፡ ብትለኝ ፡ እኔ ፡ እበላልሻለሁ ፡ እጠጣልሻለሁ ፡ ስላልኳት ፡ አስራኝ ፡ ሄደች ።

በመጨረሻው ፡ ሞት ፡ ብለው ፡ ገመዳቸውን ፡ ፈተው ፡ ጥለውት ፡ ሄዱ ። እሱም ፡ ነፍስ ፡ ሲዘራ ፡ የተደበደበው ፡ ተሰማውና ፡ እንኩዬ ፡ ጦጢት ፡ እረ ፡ አመመኝ ፡ ምን ፡ ይሻለኛል ፡ አላት ። ሂድ ፡ እዚያ ፡ ከሣሩ ፡ ላይ ፡ ተንከባለል ፡ አለችው ። እያዘገመ ፡ ተጕዞ ፡ ቢንከባለልበት ፡ ሳማ ፡ ኖሮ ፡ ለበለበው ፡ ደግሞ ፡ እንኩዬ ፡ ጦጢት ፡ እረ ፡ ባሰብኝ ፡ አለና ፡ ነገራት ። እንግዲያው ፡ ሄደህ ፡ እዚያ ፡ እመንደሩ ፡ እጠገብ ፡ ሁነህ ፡ ና ፡ ቡች ፡ ና ፡ ና ፡ ና ፡ እያልክ ፡ ተጣራ ፡ ውሾቹ ፡ መጥተው ፡ ቍስልህን ፡ ይልሱልሃልና ፡ ትድናለህ ፡ አለችው ።

እሱም ፡ እንደ ፡ መከረችው ፡ ሄዶ ፡ ና ፡ ቡች ፡ ና ፡ ቡች ፡ እያለ ፡ በተጣራ ፡ ጊዜ ፡ የመንደር ፡ ውሾች ፡ ሁሉ ፡ ተሰብስበው ፡ መጥተው ፡ ሸረክክተውና ፡ ገነጣጥለው ፡ ጨንራውን ፡ ዘርግፈው ፡ ጣሉት ፡ ይባላል ።

፨ እንኳን ፡ ደግ ፡ ለሠራ ፡ ለክፉ ፡ አድራጊም ፡ ቢሆን ፡ ቀና ፡ መሆን ፡ የተገባ ፡ ነው ። ደፋርና ፡ ጢስ ፡ መውጫ ፡ አያጣም ፡ ሆዱን ፡ ያለ ፡ ሆዱን ፡ ተወጋ ፡ እየተባለ ፡ ከባቶቻችን ፡ የሚነገረው ፡ በጦጣዋና ፡ በዝንጀሮው ፡ የተፈጸመውን ፡ ድርጊት ፡ ሊያሳስበን ፡ ይችላል ።

# የኸርብና ፡ የነብር ፡ ንስሐ ፡ አባት ፡ መያዝ ።

ነብርና ፡ ኸርብ ፡ ጕሬዛን ፡ የንስሓ ፡ አባት ፡ ያዙ ፡ ይባላል ። ነብርና ፡ ኸርብ ፡ ከዕለታት ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ በንድነት ፡ ንስሓቸውን ፡ ሊናዘዙ ፡ ከጕሬዛ ፡ ዘንድ ፡ ሄዱና ፡ አንድ ፡ በአንድ ፡ ዘርዝረው ፡ የሠሩትን ፡ በደል ፡ ሁሉ ፡ ተናገሩ ። ጕሬዛም ፡ እኔ ፡ ለራሴ ፡ ደካማ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ሰው ፡ እንደናንተ ፡ ያለ ፡ ወንበዴ ፡ ሽፍታ ፡ አልችልም ፤ ሌላ ፡ የንስሐ ፡ አባት ፡ ያዙ ፡ አስናብቻችኋለሁ፡ አላቸው ። አያ ፡ ኸርቦም ፡ አቶ፡ ነብሮም ፡ ምነው ፡ ምነው ፡ እኛ ፡ አክብረን ፡ ሽማግሌ ፡ ነው ፡ ብለን ፡ የንስሓ ፡ አባት ፡ ብናደርገው ፡ ወንበዴዎች ፡ ሽፍቶች ፡ ይበለን ! የት ፡ አባቱ ፡ በል ፡ አትጥለውም ፡ ተባባሉና ፡ ነብሮ ፡ ጕሮሮውን ፡ አንቆ ፡ ሲያደርግ ፡ አያ ፡ ኸርቦ ፡ ደግሞ ፡ እብሽሽቱ ፡ ገብቶ ፡ ግንጥልጥል ፡ አደረገው ። በዚህ ፡ አኳኋን ፡ ጕሬዛን ፡ ከገደሉ ፡ በኋላ ፡ ደግሞ ፡ ተመካከሩና ፡ የዝንጀሮ ፡ ንስሓ ፡ አባት ፡ ለመያዝ ፡ ተነሥተው ፡ ሄዱ ።

እንደ ፡ ተገናኙም ፡ በሉ ፡ ንስሐችሁን ፡ ንገሩኝ ፡ አለና ፡ ጠየቃቸው ። አያ ፡ ኸርቦም ፡ ማታ ፡ ማታ ፡ ከጐሬዬ ፡ ወጥቼ ፡ ስሰማራ ፡ ድንገት ፡ የሰው ፡ አህያ ፡ እያጋጠመኝ ፡ በልቻለሁ ፡ እንጂ ፡ ሌላ ፡ ግፍ ፡ አልሠራሁም ፡ አለው ። አቶ ፡ ነብሮም ፡ እንደዚሁ ፡ እኔም ፡ ጫካ ፡ ለጫካ ፡ ስዞር ፡ ድንገት ፡ የሰው ፡ ፍዬል ፡ እያገኘሁ ፡ በልቻለሁ ፡ እንጂ ፡ ሌላ ፡ ምንም ፡ በደል ፡ የለኝም ፡ ብሎ ፡ ነገረው ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ዝንጀሮ ፡ ሥራችሁ ፡ ይኸ ፡ ከሆነማ ፡ እናንተ ፡ መቼ ፡ ትቻላላችሁ ፤ እኔ ፡ የብዙ ፡ ልጆች ፡ አባት ፡ ነኝ ፡ ኃጢአታችሁ ፡ ከባድ ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ የናንተን ፡ ንስሓ ፡ ማስተስረያ ፡ ጊዜ አላገኝምና ፡ ሌላ ፡ አባት ፡ ፈልጉ ፡ አላቸው ። አሁንም ፡ አያ ፡ ኸርቦና ፡ አቶ ፡ ነብሮ ፡ ምክር ፡ ካደረጉ ፡ በኋላ ፡ ዝንጀሮን ፡ ይህ ፡ አታላይ ፡ ሲያላግጥብን ፡ ዝም ፡ ትለዋለህ ፡ በመባባል ፡ ለቀም ፡ አድርገው ፡ ያዙት ። ምነው ፡ ጌቶቼ ፡ ምን ፡ አጠፋሁ ፡ እያለ ፡ ዚለፈልፍም ፡ ጥርቅም ፡ አድርገው ፡ በጥብቅ ፡ አሠሩት ። እሱም ፡ እንዳለቀቁት ፡ በወቀ ፡ ጊዜ ፡ ግደሉኝ ፡ እንጂ ፡ መደብደብና ፡ መታሰር ፡ አልወድም ፡ አላቸው ። አንተን ፡ ማን ፡ ይገድላል ፡ ማሰር ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ሲሉ ፡ መለሱለት ፡ ዝንጀሮም ፡ መታሰርማ ፡ ደህና ፡ ነበር ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ገደል ፡ እንዳትሰዱኝ ፡ ብቻ ፡ አማጥኛችኋለሁ ፡ ብሎ ፡ ለመናቸው ። አያ ፡ ኸርቦና ፡ አቶ ፡ ነብሮም ፡ ደግሞ ፡ አንተ ፡ እንዳልክ ፡ ሆነና ፡ እረ ፡ በል ፡ ያዘው ፡ ይህንን ፡ አሿፊ፡ የኛን ፡ ንስሓ ፡ ያበረከተበትን ፡ ምክንያት ፡ ይንገረን ፡ አሉና ፡ በትራቸው ፡ አስ



ኪሰባበር ፡ ይዠልጡት ፡ ዠመር ። እሱም ፡ ጌቶቼ ፡ እባካችሁ ፡ በከንቱ ፡ አትድከሙ ፡ ክንዳችሁንም ፡ አይመማችሁ ፡ እኔ ፡ እንደ ፡ ሆንኩ ፡ በትር ፡ ልማዴ ፡ ነው ፡ ይልቅስ ፡ ከገደል ፡ ሳይሆን ፡ ከሁላላ ፡ ሜዳ ፡ ላይ ፡ ወስዳችሁ ፡ ጣሉኝ ፡ አለና ፡ ለመናቸው ። ደግሞ ፡ አንተ ፡ እንደ ፡ ፈለግህና ፡ እንደ ፡ መረጥክ ፡ ሆነና ፡ ብለው ፡ እንጠልጥለው ፡ ወስደው ፡ ከገደሉ ፡ አፋፍ ፡ ላይ ፡ አደረሱትና ፡ ገደል ፡ ልንጥልህ ፡ ነው ፡ እንግዲህ ፡ ንስሓችንን ፡ አስወርድልን ፡ አሉት ። አዬ ፡ እኔማ ፡ ያልኳችሁን ፡ እንቢ ፡ ብላችሁ ፡ አስራችሁ ፡ አምጥታችሁኝ ፡ የለምን ፡ ስለዚህ ፡ አሁን ፡ ገደል ፡ መጣሉ ፡ ላይቀርልኝ ፡ ምንም ፡



አቶ ፡ ነብሮና ፡ አያ ፡ ኸርቦም ፡
አንተ ፡ ለመዳን ፡ ባትፈልግ ፡
ነው ፡ ብለው ፡ የታሰረበትን ፡
ፈተው ፡ ገደል ፡ ጣሉት ።

ቢሆን ፡ ሞቴ ፡ ናትና ፡ አልነግራችሁም ፡ ሲል ፡ መለሰላቸው ። ተው ፡ ለቀቅንህ ፡ ቢሉትም ፡ ላትምሩኝ ፡ ምን ፡ ያደርግልኛል ፡ እንቢ ፡ አለና ፡ እቅጬን ፡ አስረዳቸው ። አቶ ፡ ነብሮና ፡ አያ ፡ ኸርቦም ፡ አንተ ፡ ለመዳን ፡ ባትፈልግ ፡ ነው ፡ ብለው ፡ የታሰረበትን ፡ ፈተው ፡ ገደል ፡ ጣሉት ። ዝንጀሮም ፡ ከገደሉ ፡ ተንከባሎ ፡ ወርዶ ፡ እሦስተኛው ፡ ዕርከን ፡ ላይ ፡ ሲደርስ ፡ ከቋጥኝ ፡ ላይ ፡ ቊጭ ፡ ብሎ ፡ ወደ ፡ ላይ ፡ እያየ ፡ ድዱን ፡ ገልብጦ ፡ ስቆባቸውና ፡ አልምጦባቸው ፡ ከሀመዶቹ ፡ ተቀላቀለ ።

ደግሞ ፡ ሦስተኛ ፡ አቶ ፡ ነብር ፡ አያ ፡ ኸርቦን ፡ እንግዲህ ፡ ምን ፡ ይሻለናል ፡ ትላለህ ፡ ሲል ፡ ምክር ፡ ጠየቀው ። እሱም ፡ እኔ ፡ ምን ፡ ዐውቄ ፡ ከኔ ፡

በቃ ፡ እንዳሉ ፡ ድንገት ፡ አንድ ፡ ወደል ፡ አህያ ፡ አገኛቸው ። አያ ፡ ኹ'ቦና ፡ አቶ ፡ ነብሮም ፡ ከተቀመጡበት ፡ ብድግ ፡ ብለው ፡ እንዴት ፡ ዋልክ ፡ ሲሉ ፡ ሰላምታ ፡ አቀረቡለት ። እሱም ፡ እግዚአብሔር ፡ ይመስገን ፡ ከለ ፡ በኋላ ፡ እረ ፡ ለመሆኑ ፡ ከወዴት ፡ ትመጣላችሁ ፡ አላቸው ። ዝንጀሮ ፡ ገድለን ፡ አሉት ። ምክንያቱን ፡ ለማወቅ ፡ ፈልጎ ፡ እባካችሁ ፡ ምን ፡ ቢያደርጋችሁ ፡ ነው ፡ አስረዱኝ ፡ ሲል ፡ ጠየቃቸው ። የነፍስ ፡ አባት ፡ ይዘነው ፡ የሠራነውን ፡ በደል ፡ ብንናዘዝለት ፡ ንስሓችንን ፡ ስላበረከተብን ፡ ነው ፡ ብለው ፡ ነገሩት ።

አህያም ፡ ለመሆኑ ፡ ምንድን ፡ ኖሯል ፡ ንስሓችሁ ፡ አለና ፡ ጠየቃቸው ። አያ ፡ ኹ'ቦ ፡ ያንተኑ ፡ ጓደኛ ፡ በሬ ፡ ነዋ ! ፡ ሌላማ ፡ የሠራሁት ፡ ምን ፡ ኖሮ ፡ ነው ፡ አለ ። እረ ፡ ለመሆኑ ፡ ስንት ፡ አህያ ፡ ነው ፡ የበላኸው ፡ ቢለው ፡ ዐሥር ፡ ሲል ፡ መለሰለት ። ታዲያ ፡ ዐሥራ ፡ አንድ ፡ ከልሞላህ ፡ ምን ፡ ንስሓ ፡ አለብህ ፡ አለው ። አያ ፡ ኹ'ቦም ፡ እንግዲያው ፡ አንተኑ ፡ ደግሜ ፡ ንስሓ ፡ አገባለሁ ፡ አለው ። አህያውም ፡ ያለፈውን ፡ ንስሓህን ፡ ተወጥተህ ፡ እኔን ፡ እንደ ፡ ገና ፡ አንድ ፡ አትልምን ፡ የማለት ፡ ምክር ፡ ቢያቀርብለት ፡ ሐሳቡ ፡ መልካም ፡ ነው ፡ ያለፈውን ፡ ኀጢአቴን ፡ ለማስተስረይ ፡ ከማን ፡ ዘንድ ፡ መሄድ ፡ ይሻለኛል ፡ ብሎ ፡ ጠየቀው ። ቁመታቸው ፡ አጠር ፡ መልካቸው ፡ ጠየም ፡ አፍንጫቸው ፡ ጐመድ ፡ ከራሳቸው ፡ ላይ ፡ ያለው ፡ ጥምጥማቸው ፡ ከበድ ፡ ያለ ፡ ሰው ፡ ታገኛላችሁ ። እኔም ፡ አሁን ፡ ከዚያው ፡ መምጣቴ ፡ ነው ፤ በዚህ ፡ በኩል ፡ አድርጋችሁ ፡ ሂዱ ፤ መንገዱም ፡ ቢጠፋ በችሁ ፡ እኔ ፡ ከዚሁ ፡ ሆኜ ፡ አመለክታችኋለሁ ፡ አላቸው ።

እነሱም ፡ እንደ ፡ ተነገራቸው ፡ ተነሥተው ፡ ቢሄዱ ፡ ለምድር ፡ ለሰማይ ፡ የከበዱ ፡ አዛውንት ፡ ጥምጥማቸው ፡ ያማረ ፡ አንድ ፡ ትልቅ ፡ ጠጣ ፡ ከሾላ ፡ ላይ ፡ ተቀምጠው ፡ አገኙዋቸው ። አቶ ፡ ነብሮና ፡ አያ ፡ ኹ'ቦም ፡ መሬት ፡ በመሳም ፡ እጅ ፡ ነሥተው ፡ አባታችን ፡ እንደ ፡ ምን ፡ ዋሉ ፤ አሏቸው።

ጦጣም ፡ እግዚአብሔር ፡ ይመስገን ፡ እንዴት ፡ ዋላችሁ ፡ ልጆቼ ፡ ከወዴት ፡ መጥታችኋል ፡ ብሎ ፡ ጠየቃቸው ። ከሩቅ ፡ አገር ፡ ነው ፡ ሲሉ ፡ መለሱለት ። ምነው ፡ በደኅናችሁ ፡ ነውን ፡ ቢላቸው ፡ የንስሓ ፡ ልጆች ፡ እንድንሆንም ፡ እርስዎም ፡ አባት ፡ እንዲሆኑን ፡ ብለን ፡ ነበር ። መልካም ፡ ምን ፡ ከፋኝ ፡ በሉ ፡ ትንሽ ፡ ዐረፍ ፡ በሉ ፡ አላቸው ። አቶ ፡ ነብሮና ፡ አያ ፡ ኹ'ቦም ፡ ንስሓችንን ፡ ሳንናገር ፡ አንቀመጥም ፡ ብለው ፡ አስቸገሩት ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ እንግዲያውስ ፡ ደግ ፡ ነው ፡ የሠራችሁትን ፡ ኀጢአት ፡ ዘርዝራችሁ ፡



ንገሩኝ ፡ አላቸው ። ሁለቱም ፡ ለየብቻቸው ፡ ንስሓቸውን ፡ ተናዘዙ ። እሱም ፡ ለዚህ ፡ ነው ፡ እንደዚህ ፡ የተጨነቃችሁት ፡ በሉ ፡ እንኳን ፡ መጣችሁልኝ ፡ አንድ ፡ ዕቃ ፡ እዋሻ ፡ ውስጥ ፡ አስቀምጬው ፡ የሚያወጣልኝ ፡ አጥቼ ፡ በጣም ፡ ተቸግሬ ፡ ነበረ ፡ ብሎ ፡ መጫኛውን ፡ ይዞ ፡ አቶ ፡ ነብሮንና ፡ አያ ፡ ኹ'ቦን ፡ አስከትሎ ፡ ወደ ፡ ዋሻው ፡ ሄደ ። ከገደሉም ፡ አፋፍ ፡ በደረሱ ፡ ጊዜ ፡ እንደ ፡ ምን ፡ አድርገን ፡ ነው ፡ የምንወርደው ፡ ብለው ፡ ጦጣን ፡ ጠየቁት ። እሱም ፡ አያ ፡ ኹ'ቦን ፡ አንተ ፡ ጐበዝም ፡ ደፋርም ፡ ነህ ፡ ስለዚህ ፡ እኔና ፡ አቶ ፡ ነብሮ ፡ ወገብህን ፡ በመጫኛ ፡ አስረን ፡ እንስድሃለን ፡ አንተም ፡ በእግርህ ፡ እየቈነጠጥህ ፡ ትረዳናለህና ፡ ቅር ፡ አይበልህ ። እኔ ፡ እንዳልወርድ ፡ ዐቅም ፡ የለኝ ፡ ደግሞም ፡ ሽማግሌ ፡ ነኝ ፡ አንተ ፡ ግን ፡ ጠንካራ ፡ ነህ ፡ ዕቃውም ፡ ከበድ ፡ ያለ ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ ትችለዋለህ ፡ ብሎ ፡ በስረዳው ፡ ጊዜ ፡ እሺ ፡ በማለት ፡ ትእዛዙን ፡ ተቀበለ ። ከዚህ ፡ ዘኋላ ፡ አያ ፡ ኹ'ቦን ፡ ወገቡን ፡ ጥርቅም ፡ አድርገው ፡ በመጫኛ ፡ አስረው ፡ ለቀቁት ። እሱም ፡ ከተባለው ፡ ቦታ ፡ በደረስ ፡ ጊዜ ፡ እረ ፡ ዕቃም ፡ የለ ፡ መልሳችሁ ፡ አውጡኝ ፡ አላቸው ። እነሱም ፡ ወደ ፡ ውስጥ ፡ ጠጋ ፡ ብለህ ፡ ባታይ ፡ ነው ፡ በቅጡ ፡ መርምር ፡ ብለው ፡ ተቈጡት ።

እንገቱን ፡ ወደ ፡ ውስጥ ፡ ገባ ፡ አድርጎ ፡ በሚመለከትበት ፡ ሰዓት ፡ ጦጣ ፡ እኛ ፡ ብቻችንን ፡ መጫኛውን ፡ ለመሳብና ፡ እሱን ፡ ማውጣት ፡ አንችልም ፡ ስለዚህ ፡ የንስሓ ፡ ልጆቼን ፡ ሰብስቤ ፡ እመጣና ፡ እናወጣዋለን ፤ አሁን ፡ ወደ ፡ ቤት ፡ እንሂድ ፡ አለው ። አቶ ፡ ነብሮም ፡ እውነትዎ ፡ ነው ፡ አባቴ ፡ ይኸንን ፡ ጥንበ ፡ በላ ፡ ማን ፡ ይችላል ፡ ብለው ፡ ነው ፡ አለውና ፡ መጫኛውን ፡ ለቀው ፡ ወደ ፡ ጦጣው ፡ ቤት ፡ ተነሥተው ፡ ሄዱ ።

ከቤትም ፡ በደረሱ ፡ ጊዜ ፡ ላቶ ፡ ነብሮ ፡ ግብዣ ፡ አደረገና ፡ ለመግደል ፡ ስላሰበው ፡ አሎሎ ፡ አግሎ ፡ ሞራ ፡ አልብሶ ፡ እስቲ ፡ እንድትበረታ ፡ ይኸንን ፡ የተጠበሰ ፡ ሥጋ ፡ ትንሽ ፡ ብላ ፡ በኋላ ፡ ሄደን አያ ፡ ኹ'ቦን ፡ እናወጣዋለን ፡ አለው ። አቶ ፡ ነብሮም ፡ የሥጋው ፡ ወዝ ፡ በጣም ፡ የሚያስጐመዥ ፡ ሆኖ ፡ ስላየው ፡ እነሣና ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ዋጥ ፡ አደረገው ። ወዲያው ፡ ከበሐር ፡ ሆዱ ፡ ገብቶ ፡ አንጀቱን ፡ አኰማትሮ ፡ እዚያው ፡ ድብን ፡ አድርጎ ፡ ገደለው ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ጦጣ ፡ ያቶ ፡ ነብሮን ፡ ሬሳ ፡ ደላን ፡ ሸፈነና ፡ አያ ፡ ኹ'ቦ ፡ ዘንድ ፡ ሄደ ።

ከአፋፍ ፡ ብቅ ፡ ብሎ ፡ እንደምን ፡ ዋልህ ፡ በማለት ፡ ቢጠይቀው ፡ የሠራችሁኝን ፡ ሥራ ፡ አልረሳውም ፤ ቈይ ፡ ግድ ፡ የለም ፡ ሲል ፡ ዛተበት ።

# የዥብና ፡ የዝንጀሮ ፡ መጣላት ።

ዥብና ፡ ዝንጀሮ ፡ ተጣልተው ፡ በክስ ፡ ከዳኛ ፡ ሄዱና ፡ ነገራቸውን ፡ እየዘረዘሩ ፡ አስረዱ ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ዳኛው ፡ በዝንጀሮ ፡ ብፈርድ ፡ እኽሌን ፡ ሁሉ ፡ ባንድ ፡ ቀን ፡ አጥፍቶብኝ ፡ ሰብሌ ፡ እንደ ፡ ዋለ ፡ በዱር ፡ ይቀራል ፤ በአያ ፡ ዥብ ፡ ብፈርድ ፡ ከብቶቼን ፡ ሁሉ ፡ ባንድ ፡ ቀን ፡ አዳር ፡ ይፈጅብኛል ፡ ምንም ፡ ሀብት ፡ አይተርፈኝም ፡ እንዴት ፡ ማድረግ ፡ ይሻለኛል ፡ በማለት ፡ እየተጨነቀ ፡ ነገሩን ፡ አውጥቶ ፡ አውርዶ ፡ ይህ ፡ ጉዳያችሁ ፡ በሽማግሌ ፡ የሚፈጸም ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ በኔ ፡ የሚያልቅላችሁ ፡ አይደለምና ፡ አገሌና ፡ አገሌ ፡ ያስታርቋችሁ ፡ ብሎ ፡ ወደ ፡ ሀገር ፡ ሽማግሎች ፡ ላካቸው ። ዥብና ፡ ዝንጀሮም ፡ እንደ ፡ ተነገሩት ፡ ሄደው ፡ አባቶቻችን ፡ ሆይ ፡ እኛ ፡ ሁለታችን ፡ ተጣልተን ፡ ከዳኛ ፡ ዘንድ ፡ ሄደን ፡ ነበረ ፤ የተጣላንበትን ፡ ዘርዝረን ፡ ብንነግረው ፡ ይህ ፡ ጉዳይ ፡ ሊታይ ፡ የሚገባው ፡ በሽምግልና ፡ እንጂ ፡ በዳኝነት ፡ አይደለምና ፡ እነሱ ፡ ያስማሟችሁ ፡ ስላለን ፡ ታስታርቁን ፡ ብለን ፡ መጥተናል ፡ ሲሉ ፡ ነገሯቸው ። ሽማግሎ



እነሱ ፡ ያስማሟችሁ ፡ ስላሉን ፡ ታስታርቁን ፡ ብለን ፡ መጥተናል ፡ ሲሉ ፡ ነገሯቸው ።

ችም ፡ ያያ ፡ ዥብንና ፡ ያቶ ፡ ዝንጀሮን ፡ ነገር ፡ ከሰሙ ፡ በኋላ ፡ እጅግ ፡ አድርገው ፡ አዘኑ ፡ ተበሳጩም ። ዳኛው ፡ በዝንጀሮ ፡ የፈረድኩ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ እኽሌን ፡ ሁሉ ፡ በዱር ፡ እንደ ፡ ዋለ ፡ ያስቀርብኛል ፡ በዥብም ፡ ብፈርድ ፡ ከብቶቼን ፡ ይበላብኛል ፡ ብሎ ፡ አይደለምን ፡ ወደኛ ፡ የላካቸው ። እኛም ፡ በዝንጀሮ ፡ ብንፈርድ ፡ አዝመራችን ፡ ሁሉ ፡ ባንድ ፡ ቀን ፡ ተበልቶብን ፡ ይቀራል ፤ በዥብ ፡ ብንፈርድ ፡ ከብቶቻችንን ፡ ይበላብናል ፡ በማለት ፡ ሲጨነቁ ፡ ቈይተው ፡ በማኽል ፡ አንድ ፡ ከከብትም ፡



ከእኽልም ፡ ምንም ፡ ምን ፡ የሌለው ፡ ድኻ ፡ ሽማግሌ ፡ በሀገር ፡ ውስጥ ፡ መኖሩ ፡ ትዝ ፡ አላቸውና ፡ መቼም ፡ ምኑን ፡ ይበሉበታል ፡ በማለት ፡ ከኛ ፡ ይልቅ ፡ ምክር ፡ ዐዋቂ ፡ ቃሉ ፡ ተሰሚ ፡ የሆነ ፡ አረጋዊ ፡ ሰው ፡ ስላለ ፡ ወደሱ ፡ ሂዱና ፡ ያስታርቃችሁ ፡ አሏቸው ።

መቼም ፡ የተቸገረ ፡ ጉልበቱን ፡ አይቈጥርምና ፡ ሁለቱም ፡ ተያይዘው ፡ ሄደው ፡ ለተባለው ፡ ሽማግሌ ፡ ነገሩት ። ድኻ ፡ ምን ፡ ጊዜም ፡ ቈራጥ ፡ ነውና ፤ ደግ ፡ ነው ፡ አስታርቃችኋለሁ ፡ አለና ፤ ዝንጀሮን ፡ አሁን ፡ ለጊዜው ፡ አያ ፡ ዥብን ፡ እስትጠይቀው ፡ ድረስ ፡ ወደዚያ ፡ እልፍ ፡ ብለህ ፡ ተቀመጥ ፡ አለው ። ራቅ ፡ ሲል ፡ አየና ፡ አያ ፡ ዥብ ፡ እረ ፡ ለመሆኑ ፡ እንዴት ፡ ያለህ ፡ ነህ ፡ አንተን ፡ የመሰለ ፡ ጐበዝ ፡ ከዚህ ፡ ከመላጣ ፡ ምልጥልጥ ፡ ጋራ ፡ አደባባይ ፡ ቆመህ ፡ መነጋገርህ ፡ በጣም ፡ ይገርመኛል ፤ ይደንቀኛልም ፤ ድምጥህ ፡ ጐራ ፡ ዞሮ ፡ ይሰማል ፤ ጉልበትህ ፡ ፈረስም ፡ ሆነ ፡ በቅሎ ፡ ብቻ ፡ ለብቻ ፡ ይሸከማል ፤ እንደዚህ ፡ ያለው ፡ ዠግና ፡ እንደ ፡ ምን ፡ አድርጎ ፡ ከዚህ ፡ ከሆዳም ፡ ጋራ ፡ ቆሞ ፡ ይነጋገራል ፤ ስለዚህ ፡ እሱ ፡ እንኳ ፡ ቢበድልህ ፡ አንተ ፡ ክሰህ ፡ ክብርህን ፡ ጠብቅ ፡ እንጂ ፡ ከሱ ፡ ጋራ ፡ ተቋቁመህ ፡ አትሟገት ፤ ዐርፈህ ፡ ታረቅ ፡ አለው ። አያ ፡ ዥብም ፡ እውነትህ ፡ እኮ ፡ ነው ፤ ያለ ፡ እኩያዬ ፡ ቍልቍል ፡ ወርጄ ፡ መነጋገሬን ፡ ሳስበው ፡ ያስቀቀኛል ፤ አሁንም ፡ እንደ ፡ መከርኸኝ ፡ እኔው ፡ ራሴ ፡ ክሼ ፡ መታረቁን ፡ እመርጣለሁ ፤ ከቶ ፡ ከሱ ፡ ጋራ ፡ ቆሜ ፡ ያየኝ ፡ ሁሉ ፡ ምን ፡ ብሎኝ ፡ ይሆን ፤ እያለ ፡ በመገረም ፡ ተነሥቶ ፡ ሲሄድ ፡ ዝንጀሮ ፡ በተራው ፡ ተጠራ ።

አቶ ፡ ዝንጀሮ ፡ እረ ፡ ለመሆኑ ፡ እንደ ፡ ምን ፡ ያለህ ፡ ነህ ፤ ከዚህ ፡ ከማይረባ ፡ ጥንበ ፡ በላ ፡ ጋራ ፡ በደባባይ ፡ አዛውንት ፡ መካከል ፡ ቁመህ ፡ መነጋገርህ ፡ በጣም ፡ ይገርመኛል ፤ ለመሆኑ ፡ ሰውነትህ ፡ አፈር ፡ አይልብህም ፡ አንተ ፡ እኮ ፡ ግርማህ ፡ እንደ ፡ አንበሳ ፡ የሚያስፈራ ፡ ነው ፤ በልጆችህ ፡ መካከል ፡ ሆነህ ፡ ጐምለል ፤ ጐምለል ፡ ስትል ፡ በአጀብ ፡ የሚጓዝ ፡ መኳንንት ፡ ትመስላለህ ፤ በተረተር ፡ ብቅ ፡ ባልክ ፡ ጊዜም ፡ እንደ ፡ ጦር ፡ ወርዋሪ ፡ ገበሬን ፡ ሁሉ ፡ ታሸብረዋለህ ፤ እንዲሁም ፡ ገና ፡ በሩቁ ፡ ስትታይ ፡ ያው ፡ መጣ ፡ እየተባልክ ፡ በሰው ፡ ዘንድ ፡ ታሪክ ፡ የሚነገርልህ ፡ ሆኖ ፡ ሳለ ፤ አሁን ፡ ክብርህን ፡ አዋርደህ ፡ ከዚህ ፡ ከሆዳም ፤ ከጥንብ ፡ ጐታችና ፡ ከፈሪ ፡ ጋራ ፡ በመነጋገርህ ፡ አታፍርምን ፤ እረ ፡ ምን ፡ ያለህ ፡ የማታስብ ፡ ነህ ፡ ወንድሜ ፡ በማለት ፡ ተቈጥቶ ፤ አሁንም ፡ በል ፡ ያለፈው ፡ አለፈ ፡ ለወደ ፡ ፊቱ ፡ ቢበድልህም ፡ አንተ ፡ ክሰህ ፡ ታረቅ ፤

ክብርህን ፡ አታዋርድ ፡ ብሎ ፡ ቢመክረው ፡ አቶ ፡ ዝንጀሮ ፡ አርግጥ ፡ ነው ፤ አሁን ፡ በደንብ ፡ ሆኖ ፡ ገባኝ ፡ ክብሬን ፡ በገዛ ፡ እጄ ፡ አዋርጄዋለሁና ፡ ጥፋተኛ ፡ ነኝ ፤ ክሼ ፡ መታረቁ ፡ ነው ፡ የሚሻለኝ ፡ ብሎ ፡ ሐሳቡን ፡ ተቀበለ ። ድኻው ፡ ሽማግሌ ፡ ሁለቱንም ፡ ዥብና ፡ ዝንጀሮን ፡ አንድ ፡ ላይ ፡ አቃርቦ ፡ በሉ ፡ እንግዲህ ፡ እንዳልኳችሁ ፡ ትታረቁ ፡ የለምን ፡ ብሎ ፡ ቢጠይቃቸው ፡ እሺ ፡ አሉና ፡ ለጥ ፡ ብለው ፡ እጅ ፡ ነሡ ።



እያ ፡ ዥቦ ፡ እረ ፡ ለመሆኑ ፡ እንዴት ፡ ያለህ ፡ ነህ ፡ አንተን ፡ የመሰለ ፡ ጐበዝ ፡ ከዚህ ፡ ከመላጣ ፡ ምልጥልጥ ፡ ጋራ ፡ አደባባይ ፡ ቆመህ ፡ መነጋገርህ ።



አቶ ፡ ዝንጀሮ ፡ እረ ፡ ለመሆኑ ፡ እንዴት ፡ ያለህ ፡ ነህ ፡ ከዚህ ፡ ከማያረባ ፡ ጥንብ ፡ በላ ፡ ጋራ ፡ በደባባይ ፡ አዛውንት ፡ መካከል ፡ ቆመህ ፡ መነጋገርህ ፡ በጣም ፡ ይገርማል ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ይቅር ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ተባባሉ ፡ ብሎ ፡ ይቅር ፡ አሰኝቶ ፡ አስታርቆ ፡ "በሉ ፡ ሂዱ ፡ በየቤታችሁ ፡ ግቡ ፡ ሁለተኛ ፡ ጠብ ፡ የሚባል ፡ ነገር ፡ እንዳታነሱ" ፡ ብሎ ፡ አስማምቶ ፡ አሰናበታቸው ።

፨ ልጆቼ ፡ ሆይ ፡ በገንዘብ ፡ ለሚታመኑ ፡ ሰዎች ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ መንግሥት ፡ መግባት ፡ እንዴት ፡ ጭንቅ ፡ ይሆንባቸው ፡ ተብሎ ፡ ማር ፡ ፲ ፡ ቍ ፡ ፳፬ ፡ በወንጌል ፡ ተጽፏል ። ስለዚህ ፡ ለገንዘብና ፡ ለሀብት ፡ ሳያስቡ ፡ ፍርድን ፡ መጠበቅ ፡ ለትልቅም ፡ ለትንሽም ፡ ተገቢ ፡ ተግባር ፡ ነው ።



# የአራዊት ፡ ለአንበሳ ፡ ሎሌነት ፡ ማደር ።

ነብር ፡ ዥብ ፡ ቀበሮ ፡ መጠማጥ ፡ ድመት ፡ ዝንጀሮ ፡ ዐይጥና ፡ ጦጣ ፡ እነዚህ ፡ ስምንቱ ፡ ለጌታው ፡ አንበሳ ፡ ሎሌነት ፡ አደሩ ። እያንዳንዳቸውም ፡ የተለየ ፡ ሥራ ፡ ነበራቸው ። ነብር ፡ የፍየል ፡ ዥብ ፡ የአህያ ፡ ቀበሮ ፡ የበግ ፡ መጠማጥ ፡ የዶሮ ፡ ዐይጥ ፡ የጐተራ ፡ ድመት ፡ የወተት ፡ ዝንጀሮ ፡ የውድማና ፡ የክምር ፡ ጠባቂ ፡ ጦጣ ፡ ደግሞ ፡ የልፍኝ ፡ አሽከርና ፡ ሙሉ ፡ ቤት ፡ አዛዥ ፡ በመሆን ፡ ሁሉም ፡ በየተግባራቸው ፡ ማገልገል ፡ ዠመሩ ።

እሜቴ ፡ ጦጢት ፡ እራትና ፡ ምሳ ፡ አቅራቢና ፡ አሳላፊ ፡ ስለ ፡ ሆነች ፡ ጌታዋ ፡ ከዋለበት ፡ ሲገባ ፡ ማታ ፡ ማታ ፡ ወሬ ፡ ይጠይቃት ፡ ነበር ። እሷም ፡ ተንኰለኛ ፡ በመሆኗ ፡ ለሁሉም ፡ ቅን ፡ ነገር ፡ አታስብላቸውም ፡ ነበር ።

ከዕለታት ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ ድመቶ ፡ እንቅልፍ ፡ ሲወስደው ፡ አይታ ፡ የሚጠብቀውን ፡ ወተት ፡ ከጠጣች ፡ በኋላ ፡ የተረፈውን ፡ አፍስሳ ፡ የድመቱን ፡ አፍ ፡ በወተት ፡ ለቅልቃ ፡ ሄደች ።

ጥቂት ፡ ቈይታም ፡ አውሬዎቹን ፡ ሁሉ ፡ ጠርታ ፡ አቶ ፡ ድመቶ ፡ ዛሬ ፡ ያደረገውን ፡ ኑ ፡ ጉድ ፡ እዩ ፡ አለቻቸው ። እነሱም ፡ እየሮጡ ፡ ቢሄዱ ፡ አቶ ፡ ድመቶ ፡ ከንቅልፉ ፡ ነቅቶ ፡ ምን ፡ ነከኝ ፡ እያለ ፡ አፉን ፡ በምላሱ ፡ ሲያቀላጥፍ ፡ አገኙት ። ምነው ፡ በል ፡ አንተ ፡ እንደዚህ ፡ ያለ ፡ ድፍረትና ፡ የምን ፡ አለብኝ ፡ ሥራ ፡ መሥራትህ ፡ ቢሉት ፤ ምነው ፡ ምን ፡ አጠፋሁ ፡ እንዲህ ፡ ያለ ፡ ኀይለ ፡ ቃል ፡ የምትናገሩት ፡ አላቸው ። ጌታችን ፡ ወተቱን ፡ ጠብቅ ፡ ቢልህ ፡ አንተው ፡ ትጠጣው ፡ አሉት ። እረ ፡ እኔ ፡ ከእንቅልፌ ፡ ብነሣ ፡ አፌ ፡ ወተት ፡ ወተት ፡ አለኝ ፡ እንጂ ፡ አልጠጣሁም ፡ እስቲ ፡ ጮጮው ፡ ይታይ ፡ ብሎ ፡ አውርዶ ፡ ቢያይ ፡ ምንም ፡ አጣበት ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ክች ፡ ብሎ ፡ ደነገጠና ፡ እንግዲህ ፡ ምን ፡ ይሻለኛል ፡ እባካችሁ ፡ አላቸው ። ተነሥተህ ፡ ጥፋ ፡ እንጂ ፡ ደግሞ ፡ ምን ፡ ሞያ ፡ ሠራሁ ፡ ብለህ ፡ ትጠብቃለህ ፡ ሲሉ ፡ መለሱለት ። ወዲያው ፡ ተደናግጠ ፡ ከጫካ ፡ ገብቶ ፡ ተሸሸገ ።

ጌታው ፡ አንበሳ ፡ ማታ ፡ ከዱር ፡ ሲገባ ፡ ዛሬ ፡ ቤቴና ፡ ሎሌዎቼ ፡ ሁሉ ፡ ደኅና ፡ ውለዋልን ፡ ጦጢት ፡ አላት ። አዎ ፡ ጌታዬ ፡ እኔ ፡ ዘወትር ፡ ለመናገር ፡

# ስለ ፡ አንዲት ፡ የጌታ ፡ ልጅ ፡ መፅነስ ።

አንድ ፡ ታላቅ ፡ መስፍን ፡ ሀገሩን ፡ እንደ ፡ ሠም ፡ አቅልጦ ፡ እንደ ፡ ገል ፡ ቀጥቅጦ ፡ ይገዛ ፡ ነበር ። እሱም ፡ ላቅመ ፡ ሔዋን ፡ የደረሰች ፡ አንዲት ፡ ልጅ ፡ ነበረችው ። ከዕለታት ፡ አንድ ፡ ቀንኝ አንድ ፡ ድኻ ፡ ሰው ፡ ሎሌነት ፡ ለመግባት ፡ ደብዳቤ ፡ጽፎ ፡ ከመንገድ ፡ ላይ ፡ ሲጠባበቅ ፡ መስፍኑ ፡ በበቅሎ ፡ ተቀምጦ ፡ ባጀብ ፡ ሆኖ ፡ በግርማ ፡ መጣ ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ባለጉዳዩ ፡ ወረቀቱን ፡ በንጨት ፡ አጣብቆ ፡ እያሳየ ፡ ይጮኽ ፡ ዠመር ። ጌትዮውም ፡ አጋፋሪውን ፡ ተቀበለው ፡ ብሎ ፡ ያንን ፡ ደብዳቤ ፡ አስመጥቶ ፡ ቢመለከተው ፡ ፍሬ ፡ ነገሩ ፡ ያሽከርነት ፡ ሥራ ፡ ይሰጠኝና ፡ እያገለገልኩ ፡ ልብላ ፡ የሚል ፡ ሆነ ። የሥራ ፡ችሎታውን ፡ ቢጠይቀው ፡ ያሽከርነት ፡ ሥራ ፡ በሙሉ ፡ ዐውቃለሁ ፡ አለ ። ታላቁም ፡ ገዢ ፡ ለድኻ ፡ አዛኝና ፡ ተቈርቋሪ ፡ ስለ ፡ ነበረ ፡ በልፍኝ ፡ አሽከርነት ፡ እንዲሠራ ፡ ለምድረ ፡ ግቢው ፡ አዛዥ ፡ ትእዛዝ ፡ ሰጠ ። ባለሥልጣኑም ፡ ቶሎ ፡ ብሎ ፡ የሚሠራውን ፡ ሥራ ፡ ለይቶ ፡ አስታወቀው ።



ጌትዮውም ፡ አጋፋሪውን ፡ ተቀበለው ፡ ብሎ ፡......

ከዕለታት ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ በቅልጥፍናውና ፡ በሥራ ፡ ማወቁ ፡ ተደስቶ ፡ ጌትዮው ፡ አንተ ፡ ልጅ ፡ ስምህ ፡ ማነው ፡ ብሎ ፡ ጠየቀው ። ጌታዬ ፡ ሆይ ፡ ስሜ ፡ "የኔ ፡ ነው" ፡ ሲል ፡ መለሰለት ። በማግስቱ ፡ ደግሞ ፡ ባለቤቲቷ ፡ አንተ ፡ ልጅ ፡ ስምህን ፡ ሳላውቀው ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ድረስ ፡ እንዲያው ፡ አንተ ።



ልጅ ፡ እያልኩ ፡ ነው ፡ የምጠራህ ፡ እስቲ ፡ ማን ፡ ትባላለህ ፡ ንገረኝ ፡ አሉት ፡ እመቤቱ ፡ ሆይ ፡ ስሜ ፡ "የሳቸው ፡ ነው" ፡ ብሎ ፡ በታላቅ ፡ ማክበር ፡ መለሰላቸው ። ሦስተኛ ፡ ልጃቸው ፡ ልጃገረዲቷ ፡ እንደ ፡ እናቷና ፡ እንደ ፡ አባቷ ፡ ያንን ፡ ሰው ፡ ስምህ ፡ ማነው ፡ በስምህ ፡ እንድጠራህ ፡ ብትለው ፡ "አበበ" ፡ እባላለሁ ፡ አላት ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ያ ፡ ላይን ፡ የሚያስጠይፍ ፡ ድኻ ፡ መልካም ፡ ሲበላና ፡ ደኅና ፡ ደኅና ፡ ልብስ ፡ ሲለብስ ፡ ጊዜ ፡ ሰውነቱ ፡ በጣም ፡ አማረ ፡ እንዲያውም ፡ ከነሱው ፡ ከጌቶቹ ፡ የተወለደ ፡ መሰለ ። ስለዚህም ፡ ያች ፡ ወይዘሪት ፡ ለዚያ ፡ ሰውዬ ፡ ምስጢሯን ፡ ሁሉ ፡ እየገለጠች ፡ ታጫውተው ፡ ዠመር ። ከዚህም ፡ የተነሣ ፡ ከመፅነስ ፡ ደረሰች ። አባቷና ፡ እናቷ ፡ ነፍሰ ፡ ጡር ፡ መሆኗን ፡ በተረዱ ፡ ጊዜ ፡ ገልጠሽ ፡ ንገሪን ፡ ከማን ፡ ነው ፡ ያረገዝሽው ፡ ብለው ፡ ጠየቋት ። እሷም ፡ የደፈረኝ ፡ ይህ ፡ ሎሌ ፡ ነው ፡ ያረገዝኩትም ፡ ከሱው ፡ ነው ፡ እኔ ፡ መቼስ ፡ ምን ፡ ላድርግ ፡ እናንተው ፡ በገዛ ፡ እጃችሁ ፡ ከልፍኝ ፡ አስገብታችሁ ፡ አሠለጠናችሁት ፡ አለቻቸው ። እውነቷ ፡ ነው ፡ ያደርጋል ፡ ጥፋተኞቹ ፡ እኛው ፡ ነን ፡ ያለ ፡ ልክ ፡ አቀረብነው ፡ ብለው ፡ ተናደውና ፡ ተቈጥተው ፡ ያንን ፡ አሽከር ፡ እጅ ፡ እግሩን ፡ አሳስረው ፡ ለቅጣቱ ፡ ውሳኔ ፡ ወደ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ሰደዱት ። ከዳኞቹም ፡ ፊት ፡ በቀረበ ፡ ጊዜ ፡ ግፉና ፡ በደሉ ፡ ሁሉ ፡ በነገረ ፡ ፈጅ ፡ አማካይነት ፡ በዝርዝር ፡ እንዲገለጽ ፡ ተደረገ ።

ያንን ፡ አሽከር ፡ እጅ ፡ እግሩን ፡ አሳስረው ፡ ለቅጣቱ ፡ ውሳኔ ፡ ወደ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ወሰዱት ።



ዳኞቹም ፡ ግራና ፡ ቀኙን ፡ ከዳመጡ ፡ በኋላ ፡ አንተ ፡ ሰው ፡ ይህንን ፡ ነገር ፡ ሠርተኸዋል ፡ ታምናለህ ፡ ወይስ ፡ ትክዳለህ ፡ ብለው ፡ ቢጠይቁት ፡ እኔ ፡ ድኻው ፡ በግፍ ፡ ከመታሰሬ ፡ በተቀር ፡ እንደዚህ ፡ ያለውን ፡ ድፍረት ፡ በጭራሽ ፡ አላደረግሁም ፡ ብሎ ፡ መለሰላቸው ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ እነዚህ ፡ ዳኞች ፡ ነገሩ ፡ ለፍርድ ፡ ስላስቸገራቸው ፡ የቀን ፡ ቀጠሮ ፡ አደረጉ ። ሰውዮው ፡ ግን ፡ በእስር ፡ ቤት ፡ እንዲቈይ ፡ ታዘዘ ። በነገሩ ፡ እጅግ ፡ ስላዘኑ ፡ ጒዳዩ ፡ በቶሎ ፡ ውሳኔ ፡ ያገኝ ፡ ዘንድ ፡ በማሰብ ፡ ራሳቸው ፡ መስፍኑና ፡ ባለቤቲቷ ፡ በዚያው ፡ በተቀጠረበት ፡ ቀን ፡ ልጃቸውን ፡ ይዘው ፡ ከፍርድ ፡ ቤት ፡ ቀረቡ ። ዳኞቹ ፡ ወይዘሪቷን ፡ ወደ ፡ ምርመራ ፡ ክፍል ፡ ለብቻዋ ፡ ወስደው ፡ ከማነው ፡ ያረገዝሽው ፡ ብለው ፡ ቢጠይቋት ፡ “ከአባበ” ፡ ነው ፡ ብላ ፡ መለሰችላቸው ። ደግሞ ፡ መስፍኑን ፡ ይህች ፡ ልጅ ፡ ከማን ፡ ያረገዘች ፡ ይመስልዎታል ፤ ከማንስ ፡ ይጠራጠሯታል ፡ በማለት ፡ ቢጠይቋቸው ፡ “ከኔ ፡ ነው” ፡ ደግሞ ፡ ከሌላ ፡ ከማን ፡ አረገዘች ፡ ተብሎ ፡ ይታሰባል ፡ ሲል ፡ መልስ ፡ ሰጣቸው ። ደግሞ ፡ ሦስተኛ ፡ ባለቤቲቱን ፡ መቼም ፡ ምንም ፡ ቢሆን ፡ ልቦናዎ ፡ ሳያውቅ ፡ አይቀርምና ፡ ይህች ፡ ልጅዎ ፡ ከማን ፡ ያረገዘች ፡ ይመስልዎታል ፤ ይህ ፡ ነገር ፡ ስላስቸገረን ፡ የሚጠረጥሩትን ፡ ሰው ፡ ይንገሩን ፡ አሏቸው ። ከሌላ ፡ ከማንም ፡ ሰው ፡ አላረገዘች ፡ “ከሳቸው ፡ ነው” ፡ ብለው ፡ አረጋገጡላቸው ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ዳኞቹ ፡ ፊታቸውን ፡ ወደ ፡ እናትና ፡ አባቷ ፡ መልሰው ፡ ታዲያ ፡ ይህ ፡ ድኻ ፡ ምን ፡ ያድርገን ፡ ብላችሁ ፡ ነው ፡ እናንተው ፡ እያወቃችሁ ፡ በመናችሁት ፡ ጥፋት ፡ ያሰራችሁት ፡ እውነትም ፡ በሥልጣናችሁ ፡ ተመክታችሁ ፡ ነው ፡ በሉ ፡ አሁንም ፡ ያላገባብ ፡ በግፍ ፡ ስላሰራችሁት ፡ ሙሉ ፡ ካሳ ፡ እንዲሰጠው ፡ ወስነናል ። እርስዎም ፡ ጌታዬ ፡ ሕግ ፡ የማይፈቅደውን ፡ መጽሐፍ ፡ የማያዘውን ፡ ተግባር ፡ ሠርተው ፡ ስለ ፡ ተገኙ ፡ እስራት ፡ ይገባዎታልና ፡ ወደ ፡ ወህኒ ፡ እንዲሄዱ ፡ ፈርደናል ፡ ብለው ፡ ድኻውን ፡ በገንዘብ ፡ አስክሰው ፡ ለቀቁት ፡ ይባላል ።

፨ ካያያዝ ፡ ይቀደዳል ፤ ከነጋገር ፡ ይፈረዳል ፡ እየተባለ ፡ የሚተረተውም ፡ እንደዚህ ፡ ያለ ፡ ነገር ፡ በጋጠመ ፡ ጊዜ ፡ መሆኑን ፡ ተገንዝበ ፡ መጠንቀቅ ፡ ይገባል ።



# ስለ ፡ አንድ ፡ ታማኝ ፡ አሽከር ።

ባንድ ፡ አገር ፡ ውስጥ ፡ ጌታው ፡ እጅግ ፡ አድርጎ ፡ የሚያምነው ፡ እሱም ፡ ጌታውን ፡ የሚወድ ፡ የሚያከብርና ፡ የሚፈራ ፡ አሽከር ፡ ነበር ። በሚያደርገውና ፡ በሚሠራውም ፡ ሁሉ ፡ የተጠነቀቀ ፡ ፈሪሀ ፡ እግዚአብሔር ፡ ያደረበት ፡ በመሆኑ ፡ ጌታው ፡ ወደ ፡ ዘመቻ ፡ ሲሄድ ፡ አንተ ፡ እኔን ፡ በማገልገል ፡ የደከምህ ፡ ፈቃዴን ፡ የምትፈጽም ፡ ታማኝ ፡ አሽከሬ ፡ እኔ ፡ ከጦርነት ፡ እስክመለስ ፡ ድረስ ፡ ቤቴ ፡ እንዳይቀዘቅዝ ፡ ግቢዬ ፡ እንዲከበር ፡ ሚስቴ ፡ እንድትታፈር ፡ በጥብቅ ፡ አደራ ፡ እልሃለሁ ። ይህንን ፡ የመሰለ ፡ አደራ ፡ የሚሰጠው ፡ እጅግ ፡ ለተወደደና ፡ ለታመነ ፡ አሽከር ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ለማንም ፡ ሰው ፡ አይደለምና ፡ አስብበት ፡ አለና ፡ አስገነዘበው ።

ይህም ፡ አሽከር ፡ አደራው ፡ እጅግ ፡ ስለ ፡ ከበደውና ፡ ከዚህም ፡ በላይ ፡ አሳዳሪውን ፡ እንደ ፡ ራሱ ፡ አድርጎ ፡ ይወደው ፡ ስለ ፡ ነበረ ፤ ጌታዬ ፡ እርስዎ ፡ ወደ ፡ ሞት ፡ አገር ፡ ሲሄዱ ፡ እኔ ፡ መቅረት ፡ አይገባኝም ፡ ሲሆን ፡ እንደ ፡ ጋሻ ፡ ከፊትዎ ፡ ተመክቼ ፡ ጦር ፡ ቀማሽ ፡ መሆን ፡ አለብኝ ፤ ሴት ፡ ይመስል ፡ ከቤት ፡ መዋል ፡ ግን ፡ አይገባኝም ፡ ብሎ ፡ መልስ ፡ ሰጠው ። ጌትዮው ፡ ግን ፡ ያለሱ ፡ ላደራ ፡ የሚበቃ ፡ ሰው ፡ በቤቱ ፡ ስላልነበረው ፡ ንብረቱን ፡ እንዲጠብቅለት ፡ በልመና ፡ ጭምር ፡ አስገድዶ ፡ ወዲያውም ፡ አስምሎ ፡ ቀጥሎ ፡ ባለው ፡ ሁናቴ ፡ ሲሠራ ፡ እንዲቈየው ፡ አዘዘ ። ቃሉም ፡ እንደኛ ፡ እልፍኙ ፡ ካለበት ፡ ቅጥር ፡ ግቢ ፡ ማንም ፡ ሰው ፡ እንዳይገባ ፤ ሁለተኛ ፡ አንተም ፡ ላንድ ፡ አፍታ ፡ እንኳን ፡ ቢሆን ፡ ከበር ፡ ሳትለይ ፡ ሌት ፡ ከቀን ፡ እንድትጠብቅ ፤ ሦስተኛ ፡ ባለቤቴ ፡ በለቅሶም ፡ ሆነ ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ምክንያት ፡ ከግቢዬ ፡ እንዳትወጣ ፤ አራተኛ ፡ ሚስቴ ፡ ካለችበት ፡ ቦታ ፡ “ሰው ፡ ማመኔ” ፡ ከምትባለዋ ፡ ገረዴ ፡ በስተቀር ፡ ሌላ ፡ ማንም ፡ ሰው ፡ ቢሆን ፡ እንዳይገባ ፡ ጠንክረህ ፡ ከልክል ፡ የሚል ፡ ነው ።

ለሚስቱም ፡ ይህንኑ ፡ አስረድቶ ፡ ነግሮ ፡ ተነሥቶ ፡ ወደ ፡ ዘመቻው ፡ ሄደ ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ታማኙ ፡ ሎሌ ፡ ከተቀበለው ፡ ትእዛዝ ፡ አንዳች ፡ ነገር ፡ ሳያዛንፍና ፡ ሳያቃውስ ፡ እንደ ፡ ተባለው ፡ ሁሉ ፡ በትክክል ፡ ብዙ ፡ ቀን ፡ ሲጠብቅ ፡ ቈየ ። ነገር ፡ ግን ፡ የደጎና ፡ ሰው ፡ ተቃዋሚ ፡ ብዙ ፡ ነውና ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ እመቤቲቱ ፡ ሲሆን ፡ ከውጪ ፡ የሚያነጋግረኝ ፡ ሰው ፡ አስገባልኝ ፡ ካልሆነም ፡ አንተ ፡ እየገባህ ፡ አጫውተኝ ፡

# ሁለት ፡ አታላዮች ።

በንድ ፡ አገር ፡ ውስጥ ፡ ሰውን ፡ ሁሉ ፡ የሚያታልሉና ፡ የሚያከስሩ ፡ ሁለት ፡ ሰዎች ፡ ነበሩ ። ከዕለታት ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ አንደኛው ፡ ማር ፡ በዶጮ ፡ ሁለተኛው ፡ ደግሞ ፡ ቅቤ ፡ በፍላል ፡ ይዘው ፡ ሁለቱም ፡ እገበያ ፡ ተገናኙ ። በዚህም ፡ ጊዜ ፡ ባለማሩ ፡ ባለቅቤውን ፡ ወንድም ፡



ባለማሩ ፡ ባለቅቤውን ፡ ወንድም ፡ ምን ፡ ይዘሃል ፡ አለው ።

ምን ፡ ይዘሃል ፡ አለው ። እሱም ፡ ቅቤ ፡ ነዋ ፡ ሲል ፡ መለሰለት ። በምን ፡ ይለወጣል ፡ ቢለው ፡ በማር ፡ አለው ። እንግዲያው ፡ እኔ ፡ ማር ፡ ይዠለሁና ፡ እንላወጥ ፡ ብሎ ፡ ቢጠይቀው ፡ እሺ ፡ እኔም ፡ የምፈልገው ፡ ይኸንኑ ፡ ነበረ ፡ በማለት ፡ ተስማምተው ፡ እንደ ፡ ተመረገ ፡ ሳይከፍቱ ፡ ተለዋወጡ ። የማሩ ፡ ጌታ ፡ ዶጮውን ፡ ከንገቱ ፡ በታች ፡ አተላ ፡ ከንገቱ ፡ በላይ ፡ ማር ፡ የቅቤውም ፡ ጌታ ፡ አፍላሉን ፡ ከንገቱ ፡ በላይ ፡ ቅቤ ፡ ከንገቱ ፡ በታች ፡ እበት ፡ አድርገው ፡ መርገው ፡ ኖሮ ፡ የማሩም ፡ ጌታ ፡ እኔ ፡ አታለልኩት ፡ የቅቤውም ፡ ጌታ ፡ እኔ ፡ አታለልኩት ፡ በማለት ፡ ሁለቱም ፡ ደስ ፡ ደስ ፡ እያላቸው ፡ ሌላውን ፡ ጕዳያቸውን ፡ ትተው ፡ እየተሸከሙ ፡ ወደ



የሰፈራቸው ፡ ሄዱ ። እቤታቸውም ፡ በደረሱ ፡ ሰዓት ፡ እየከፈቱ ፡ ቢያዩት ፡ የማሩ ፡ አተላ ፡ የቅቤውም ፡ እበት ፡ ሆነባቸው ። በዚህም ፡ ጊዜ ፡ ባለማሩ ፡ ባለቅቤውን ፡ ይህስ ፡ ከኔ ፡ የበለጠ ፡ ነውና ፡ አግኝቼው ፡ ጓደኛ ፡ በሆነኝ ፡ አለና ፡ ተመኘ ።

ዳግመኛ ፡ ባለማሩ ፡ ጌሾ ፡ የሚመስለውን ፡ ጠዶ ፡ የሚባለውን ፡ ቅጠል ፡ ቀርጥፎ ፡ አድርቆ ፡ በስልቻው ፡ አዘጋጅቶ ፡ በናቱ ፡ ላይ ፡ የጌሾ ፡ ቅጠል ፡ አድርጎ ፡ ይዞ ፡ ወደ ፡ ገበያ ፡ ወጣ ።

ሁለተኛውም ፡ አታላይ ፡ ሲናር ፡ በውስጥ ፡ ገብስ ፡ በላይ ፡ አድርጎ ፡ በስልቻ ፡ ይዞ ፡ እገበያ ፡ ሄደ ። ሁለቱም ፡ ሳይተዋወቁ ፡ ተገናኙ ። የጠዶው ፡ ጌታ ፡ ጌሾ ፡ በገብስ ፡ የሚለውጥ ፡ እያለ ፡ ሲዞር ፡ ባለሲናሩ ፡ ና ፡ ወደኔ ፡ አለው ።

—ልውጫውሳ ፤

—መሳ ፡ ለመሳ ።

—ሸልቻውሳ ፤

—እኔም ፡ ያንተን ፡ አንተም ፡ የኔን ፡ አንሣ ፡ ተባብለው ፡ ሁለቱም ፡ ተለዋውጠው ፡ ይዘው ፡ ሄዱ ። እየቤታቸው ፡ ሲደርሱ ፡ ቢፈቱት ፡ የባለጌሾው ፡ ጠዶ ፡ ቅጠል ፤ የባለገብሱም ፡ ሲናር ፡ ሆነባቸው ። ሁለቱም ፡ በየበኩላቸው ፡ ሲናደዱ ፡ ሲጨሱ ፡ ውለው ፡ ቈይ ፡ ግድ ፡ የለም ፡ እሱ ፡ እንደ ፡ ተጫወተብኝ ፡ ሳልጫወትበት ፡ በማለት ፡ በየበኩላቸው ፡ ሲፎክሩ ፡ ሰነበቱ ።

ሦስተኛ ፡ ጊዜ ፡ ደግሞ ፡ አንደኛው ፡ ገንዘብ ፡ ሁለተኛው ፡ ዕውር ፡ አህያ ፡ ይዘው ፡ እገበያ ፡ ወጡ ። ያነን ፡ አህያ ፡ ባለወርቁ ፡ ይሸጣል ፡ ወይ ፡ ብሎ ፡ ባለቤቱን ፡ ጠየቀው ። እሱም ፡ አዎን ፡ ቢለው ፡ ዋጋውን ፡ ንገረኝ ፡ አለው ።

—ኻያ ፡ ብር ።

—ርግጡሳ ፤

—ወርቅ ፡ ሲመጣ ። አህያው ፡ ታስሮ ፡ ነበረና ፡ ፍታውና ፡ እንየው ፡ ቢለው ፡ አይፈታም ፡ የተፈታ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ አለቤቱ ፡ አይቆምም ፡ አለው ።

—እንግዲያው ፡ ምን ፡ ማድረግ ፡ ይሻላል ፧

ሁለት ፡ ሆናችሁ ፡ አንዳችሁ ፡ ከፊት ፡ አንዳችሁ ፡ ከኋላ ፡ በገመድ ፡ ካልሳባችሁት ፡ አምልጦ ፡ ይጠፋል ፤

—እሺ ፡ ዋጋውን ፡ በደንብ ፡ ንገረኝ ።

—መቼስ ፡ ምን ፡ ይደረጋል ፡ ይሁን ፡ ባሥራ ፡ ስድስት ፡ ብር ፡ ግዛው ። በዚሁ ፡ ተስማምተው ፡ ያም ፡ ሰውዬ ፡ ዕውር ፡ አህያ ፡ ባሥራ ፡ ስድስት ፡ ብር ፡ ገዛና ፡ እቤቱ ፡ ሲደርስ ፡ ቢለቀው ፡ አህያው ፡ የሰው ፡ ኰቴ ፡ እየሰማ ፡ ወደ ፡ ቤት ፡ ሮጦ ፡ ጥልቅ ፡ አለ ። እቤትም ፡ ከገባ ፡ ወዲያ ፡ ምንም ፡ ውጣ ፡ እያሉ ፡ ቢደበድቡትና ፡ ቢጠዝሉት ፡ ዕውር ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ ወደ ፡ ሴቶቹ ፡ ይሄድ ፡ ዠመር ። እነሱም ፡ የሚነክሳቸው ፡ መስሏቸው ፡ ሸሽተው ፡ ወደ ፡ ውጭ ፡ ሮጡ ፤ በዚህ ፡ ጊዜ ፡ አህያው ፡ እያሸተተ ፡ እንዳ ፡ ገብቶ ፡ በሌማቱ ፡ ላይ ፡ ያለውን ፡ እንጀራ ፡ ልቅም ፡ አድርጎ ፡ በላው ።



መቼስ ፡ ምን ፡ ይደረጋል ፡ ይሁን ፡ ባሥራ ፡ ስድስት ፡ ብር ፡ ግዛው ።

ባለቤቲቱ ፡ የሆነውን ፡ አይታ ፡ ቶሎ ፡ ብላ ፡ ባሏን ፡ ጠራችውና ፡ በቍጣ ፡ ቃል ፡ ና ፡ ያመጣኸውን ፡ አህያ ፡ አስወጣልኝ ፡ አለችው ። ሰውዬውም ፡ ከቤት ፡ ገባና ፡ ከወደ ፡ ኋላው ፡ ዞሮ ፡ በዱላ ፡ ይመታው ፡ ዠመር ፤ አህያው ፡ ግን ፡ ዕውር ፡ በመሆኑ ፡ በሩ ፡ ስለ ፡ ጠፋው ፡ ቢጨንቀው ፡ የኋላ ፡ እግሩን ፡ እየሰነዘረ ፡ መራገጥ ፡ ያዘ ። ስለዚህም ፡ ሰውዬው ፡ ጥሎ ፡ ሸሸ ። ቢሆንም ፡ እንስሳው ፡ ዝላዩን ፡ ስለ ፡ ቀጠለ ፡ ጋኑን ፡ ድስቱን ፡ ማሰሮውን ፡ ጭንቍላውን ፡ ሙሃቻውን ፡ ዋዲያቱን ፡ ሁሉ ፡ ሰባብሮ ፡ በሙሉ ፡ የቤቱን ፡ ዕቃ ፡ ፈጀው ። ሰዎቹም ፡ ዐይኑ ፡ እያየ ፡ ያሸነፋቸው ፡ መስሏቸው ፡ በጕራ ፡ ደብድበው ፡ ገደሉት ።



አራተኛ ፤ ይህ ፡ ሰው ፡ ለምን ፡ ተሸነፍኩ ፡ ብሎ ፡ ተናዶ ፡ እንደ ፡ ገና ፡ ተነሥቶ ፡ እገበያ ፡ ቢወጣ ፡ አሁንም ፡ ያኑኑ ፡ ሰው ፡ አህያ ፡ ሲሸጥ ፡ አገኘው ። ዛሬስ ፡ አለቀውም ፡ ብሎ ፡ ዘዴ ፡ ፈጥሮ ፡ ብድሩን ፡ ሊመልስ ፡ ማር ፡ ፈልጎ ፡ ገዛና ፡ ላንዱ ፡ በልንጀራው ፡ ሐሳቡን ፡ ገለጠለት ። ጓደኛውም ፡ በጕዳዩ ፡ ተስማማበትና ፡ ባንድነት ፡ ሄደው ፡ አህያ ፡ ሽጥልን ፡ አሉት ። እሱም ፡ ግዙ ፡ አላቸው ። ዋጋውስ ፡ ቢሉት ፡ ዐሥራ ፡ አራት ፡ ብር ፡ አለ ። ዋጋ ፡ በዛ ፡ ብሎ ፡ አንደኛው ፡ ብሩን ፡ ይዞ ፡ ሲከራከር ፡ ሌላው ፡ ጠጋ ፡ ብሎ ፡ አህያው ፡ አፍ ፡ ውስጥ ፡ ማር ፡ ጨመረበት ። ላህያ ፡ ማር ፡ አይጥማት ፡ እንደ ፡ ተባለው ፡ ያ ፡ አህያ ፡ መረረውና ፡ ለሀጩን ፡ ያንጠባጥብ ፡ ዠመር ፤ መላሱም ፡ ተጕለጐለ ፤ በዚህ ፡ ጊዜ ፡ እነዚያ ፡ ሰዎች ፡ አይ ፡ አይ ፡ መጋኛ ፡ መቶት ፡ ለሞት ፡ የደረሰውን ፡ አህያ ፡ ነው ፡ ይህንን ፡ ያኽል ፡ ገንዘብ ፡ አውጥታችሁ ፡ ግዙኝ ፡ የምትለን ፡ ከቶ ፡ ማን ፡ ይታለልልሀ ፡ መሰለህ ፡ ወንድሜ ፡ እያሉ ፡ አስደነገጡት ። እሱም ፡ አተኵሮ ፡ ቢያየው ፡ እውነትም ፡ የሚሞትበት ፡ መሰለው ። ባለ ወርቆቹ ፡ መለሱና ፡ በል ፡ ሽጥልን ፡ ቢድንም ፡ መልከም ፡ ቢሞትም ፡ በዕድላችን ፡ እናዝናለን ፡ አሉት ። እሺ ፡ ግዙ ፡ አለ ።

—ምን ፡ ያኽል ፧

—ሦስት ፡ ብር ፤

—ሁለቱን ፡ ትተህ ፡ አንድ ፡ ብር ፡ አትሸጥልንም ፧

—ይሁን ፡ አምጡ ።

አንድ ፡ ብር ፡ ሰጥተው ፡ አህያቸውን ፡ ይዘው ፡ ወደ ፡ ቤታቸው ፡ ሄዱ ። አህያው ፡ ግን ፡ ሕመም ፡ የለበትም ፡ ነበርና ፡ ውሃ ፡ በጠጣ ፡ ጊዜ ፡ ደኅና ፡ ሆነ ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ሁለቱም ፡ አታላዮች ፡ በሥራቸው ፡ ስለ ፡ ተዋወቁ ፡ እንግዲህ ፡ ጓደኛ ፡ እንሁን ፡ አብረን ፡ የሆን ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ እንከብራለን ፡ ተባብለው ፡ ምክር ፡ አደረጉ ። በሐሳቡም ፡ ተስማምተው ፡ አንደኛው ፡ እንግዲህ ፡ ወንድሜ ፡ ተነሥተን ፡ ለሌብነት ፡ ወደ ፡ ሩቅ ፡ አገር ፡ እንሂድ ፡

እሷም ፡ ሄዳ ፡ በሩን ፡ ትም ፡ ትም ፡ አደረገች ። እግዚአብሔርም ፡ ብቅ ፡ አለና ፡ ምን ፡ ሆንሽ ፡ ምንስ ፡ ትፈልጊያለሽ ፡ ብሎ ፡ ጠየቃት ። ልጅ ፡ ትሰጠኝ ፡ ብዬ ፡ ነው ፡ አለችው ። የተቈለፈ ፡ አገልግል ፡ አምጥቶ ፡ እንቺ ፡ ይህንን ፡ ይዘሽ ፡ ሄደሽ ፡ አገርሽ ፡ ለመድረስ ፡ ስትቃረቢ ፡ ውዝ ፡ ውዝ ፡ አድርገሽ ፡ ክፈችው ፡ አለና ፡ ሰጣት ። አገልግሉን ፡ ተቀብላ ፡ ይዛ ፡ ሄዳ ፡ አገሯ ፡ ለመግባት ፡ ትንሽ ፡ ሲቀራት ፡ ውዝ ፡ ውዝ ፡ አድርጋ ፡ ብትከፍተው ፡ ከውስጡ ፡ ምን ፡ የመሰለ ፡ ወንድ ፡ ልጅ ፡ አገኘች ። በዚህ ፡ ጊዜም ፡ የነበራት ፡ ደስታና ፡ ለፈጣሪዋ ፡ ያቀረበችው ፡ ምስጋና ፡ ይህ ፡ ነው ፡ ተብሎ ፡ ሊገመት ፡ የሚቻል ፡ አልነበረም ። በመጨረሻውም ፡ ልጅዋን ፡ አዝላ ፡ ከቤቷ ፡ ገባች ።

ወዲያው ፡ ያች ፡ ቂል ፡ ሴት ፡ ልጅሽን ፡ ከወዴት ፡ አገኘሽው ፡ አለቻት ፤ እሷም ፡ እግዚአብሔር ፡ ሰጠኝ ፡ ብላ ፡ መለሰችላት ።

—እስቲ ፡ አባክሽ ፡ ቤቱን ፡ ለኔም ፡ አሳይኝ ፤

—ሂጂ ፡ ያች ፡ ውሃ ፡ የምትቀዳ ፡ ሴት ፡ ታሳይሽ ።

እንደ ፡ ተነገራት ፡ ሄደችና ፡ አንቺ ፡ ሴት ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቤት ፡ አሳይኝ ፡ ብላ ፡ ጠየቀቻት ። እሷም ፡ ውሃ ፡ ቅጂልኝና ፡ አለቻት ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ያንቺ ፡ ውሃ ፡ ቀጂ ፡ ነኝ ፡ ብላ ፡ ተቈጣቻት ። እንግዲያውስ ፡ ሂጂ ፡ ያች ፡ ኩበት ፡ ለቃሚ ፡ ሴት ፡ ታሳይሽ ፡ በማለት ፡ ስለ ፡ መለሰችላት ፡ ወደርሷ ፡ ቀርባ ፡ አንቺ ፡ ሴት ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቤት ፡ አሳይኝ ፡ ብላ ፡ ጠየቀቻት ። ኩበት ፡ ልቀሚልኝና ፡ ስትል ፡ መለሰችላት ። አሁንም ፡ ያንቺ ፡ ኩበት ፡ ለቃሚ ፡ ነኝ ፡ ወይ ፡ ብላ ፡ በኀይለ ፡ ቃል ፡ ተናገረች ። በይ ፡ ተይው ፡ እኅቴ ፤ ያ ፡ ማር ፡ የሚያግዘው ፡ ሰው ፡ ያሳይሽ ፡ ወደ ፡ ርሱ ፡ ሂጂ ፡ አለቻት ። እሺ ፡ ብላ ፡ ስትገናጀብ ፡ ሄዳ ፡ ብትጠይቀው ፡ እንደ ፡ ፊተኛው ፡ ይህንን ፡ ማር ፡ አግዢልኝና ፡ አላት ። እሷም ፡ ምነው ፡ እኔ ፡ ያንተ ፡ ማር ፡ ተሸካሚ ፡ ነኝን ፡ አለችው ። በይ ፡ እንግዲያው ፡ ሂጂ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ ድም ፡ ድም ፡ የሚለው ፤ የሰይጣን ፡ ቤት ፡ ቅጭል ፡ ቅጭል ፡ የሚለው ፡ ነው ፡ ሲል ፡ አመለከታት ። ሄዳ ፡ ድም ፡ ድም ፡ የሚለውን ፡ ብትመታው ፡ ሰይጣን ፡ ብቅ ፡ አለና ፡ ምን ፡ ልታደርጊ ፡ መጣሽ ፡ አላት ። ልጅ ፡ ትሰጠኝ ፡ ብዬ ፡ ነው ፡ ስትል ፡ መልስ ፡ ሰጠችው ። የተቈለፈ ፡ አገልግል ፡ አምጥቶ ፡ ይህንን ፡ ይዘሽ ፡ ሄደሽ ፡ ከጠራ ፡ ሜዳ ፡ ላይ ፡ ስትደርሽ ፡ ውዝ ፡ ውዝ ፡ አድርገሽ ፡ ክፈችው ፡ አለና ፡ ሰጣት ። እሷም ፡ ደስ ፤ ተሰኝታ ፡



እንዳዘዛት ፡ ዕቃውን ፡ ይዛ ፡ ሄዳ ፡ ከጠራ ፡ ሜዳ ፡ ላይ ፡ ስትደርስ ፡ ብትከፍተው ፡ ከውስጡ ፡ ዘንዶ ፡ ወጣ ። ደንግጣና ፡ ፈርታ ፡ ብትሸሽም ፡ ስለ ፡ ተከተላት ፡ ብዙ ፡ ሰዎች ፡ በቅሎ ፡ ጭነው ፡ በመንገድ ፡ ሲያልፉ ፡ አገኘችና ፡ እናንተ ፡ ሰዎች ፡ እባካችሁ ፡ ስለ ፡ ነፍስ ፡ ከዘንዶ ፡ አድኑኝ ፡ አለቻቸው ።

እነሱም ፡ እሺ ፡ ብለው ፡ ከከብቶቹ ፡ መካከል ፡ ግቢ ፡ አሏት ፡ ወዲያው ፡ ያ ፡ ዘንዶ ፡ ደረሰና ፡ ባወጣላት ፡ ስም ፡ "ተልባ ፡ ተልቢቱን" ፡ አሳዩኝ ፡ ሳልውጣችሁ ፡ ሳልሰለቅጣችሁ ፡ ብሎ ፡ ሰዎቹን ፡ አስፈራራቸው ። እነሱም ፡ አደጋውን ፡ ሠግተው ፡ ያችውልህ ፡ ከበቅሎቹ ፡ ውስጥ ፡ አሉት ። ከዚያ ፡ ደግሞ ፡ ተነሥታ ፡ ስትሮጥ ፡ እሱም ፡ ሲከተል ፡ በጎች ፡ የሚያግዱ ፡ ልጆች ፡ አገኘችና ፡ እናንተ ፡ ልጆች ፡ እባካችሁ ፡ ከዘንዶ ፡ አድኑኝ ፡ አለቻቸው ። እነሱም ፡ ከበጎቹ ፡ ውስጥ ፡ ገብታ ፡ እንድትሸሸግ ፡ አመለከቷት ። እበጎቹ ፡ ውስጥ ፡ ከመግባቷ ፡ ያ ፡ ዘንዶ ፡ ሲሮጥ ፡ መጣና ፡ እናንተ ፡ ልጆች ፡ ዛሬ ፡ ተልባ ፡ ተልቢቱን ፡ ባታሳዩኝ ፡ ልብ ፡ አድርጉ ፡ አለቃችሁም ፡ እውጣችኋለሁ ፡ እሰለቅጣችኋለሁ ፡ ሲል ፡ ዛተባቸው ። ያችውልህ ፡ ብለው ፡ ስለ ፡ ገለጹለትም ፡ ወደ ፡ በጎቹ ፡ መካከል ፡ ገባ ፡ አሁንም ፡ ሽሽታ ፡ አጥብቃ ፡ አምራ ፡ ስትሮጥ ፡ አቶ ፡ ዐይጦ ፡ ሰናፊሉን ፡ ባጭር ፡ ታጥቆ ፡ ዐውድማ ፡ ጥሎ ፡ ጤፍ ፡ ሲወቃ ፡ አገኘችውና ፡ አቶ ፡ ዐይጦ ፡ እባክህ ፡ ከዘንዶ ፡ አድነኝ ፡ ብላ ፡ ለመነችው ። ገረድ ፡ ትሆኚኝ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ነዋ ፡ አላት ። እሷም ፡ ተጨንቃለችና ፡ እሺ ፡ እሆንሃለሁ ፡ ብላ ፡ መለሰችለት ። ስለዚህ ፡ በይ ፡ ጥቂት ፡ ስረፊ ፡ ብሎ ፡ ከጕሬው ፡ አስገብቶ ፡ አስቀመጣትና ፡ ወደ ፡ ጤፉ ፡ ውቂያው ፡ ተመለሰ ። ያም ፡ ዘንዶ ፡ ተከትሎ ፡ ሲምዘገዘግ ፡ ደረሰና ፡ አቶ ፡ ዐይጦ ፡ ተልባ ፡ ተልቢቱን ፡ አሳየኝ ፡ ሳልውጥህ ፡ ሳልሰለቅጥህ ፡ አለው ። ታዲያ ፡ ብትውጠኝ ፡ ብትሰለቅጠኝ ፡ ዱብ ፡ እላለሁ ፡ እንጂ ፡ ሌላ ፡ ምን ፡ እሆናለሁ ፡ ብለህ ፡ ነው ፡ አለው ። ስለዚህም ፡ በመልሱ ፡ ተናዶ ፡ ለቀም ፡ አድርጎ ፡ ጐረሠው ።

አቶ ፡ ዐይጦም ፡ እንዳለው ፡ ሁሉ ፡ ከመ ፡ ቀጽበት ፡ ሾልኮና ፡ በቂጡ ፡ ዱብ ፡ አለ ። እንዲህ ፡ ከሆነ ፡ ቄይ ፡ ግድ ፡ የለም ፡ አታመልጠኝም ፡ ብሎ ፡ በጭድ ፡ ቂጡን ፡ ጠቅጥቆ ፡ ዋጥ ፡ አደረገው ። አቶ ፡ ዐይጦም ፡ ሳይታይ ፡ ቶሎ ፡ ብሎ ፡ ጩቤውን ፡ ታጥቆ ፡ ነበርና ፡ ከባሕር ፡ ሆዱ ፡ ሲደርስ ፡ ቀዶ ፡ በጐኑ ፡ ወጣ ። ዘንዶው ፡ የዋጣቸውም ፡ ሰዎች ፡ ሁሉ ፡ እንዲሁ ፡ ከሆዱ ፡ ውስጥ ፡ ውልቅ ፡ ውልቅ ፡ አሉ ።

# እግዜር ፡ ሞት ፡ ክረምትና ማደሪያ ፡ እንደ ፡ ለመኑ ።

እግዜር ፡ ክረምት ፡ ሞት ፡ ሦስቱ ፡ ባንድነት ፡ ሲጓዙ ፡ ውለው ፡ ስለ ፡ መሸባቸው ፡ ካንድ ፡ ሰው ፡ ቤት ፡ ሄዱና ፤ እግዜር ፡ ቤቶች ፡ እንዴት ፡ ዋላችሁ ፡ አለ ። ሰውዬውም ፡ እግዚአብሔር ፡ ይመስገን ፡ እንደ ፡ ምን ፡ ዋልክ ፡ በማለት ፡ መለሰለት ። እባካችሁ ፡ የመሸብን ፡ መንገደኞች ፡ ነንና ፡ አውሬ ፡ እንዳይበላን ፡ አሳድሩን ፡ ብሎ ፡ ለመነ ። አንተ ፡ ማነህ ፤ ከወዴት ፡ መጥተሃል ፡ ሲል ፡ ባለቤቱ ፡ ጠየቀ ። እሱም ፡ እኔ ፡ እግዜር ፡ ነኝ ፡ አለው ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ያ ፡ ሰው ፡ ከተቀመጠበት ፡ ብድግ ፡ አለና ፡ ሽመሉን ፡ መዞ ፡ አንተ ፡ አድላዊ ፡ አንዱን ፡ ጌታ ፡ አንዱን ፡ ድሃ ፡ አንዱን ፡ በሽተኛ ፡ አንዱን ፡ ጤነኛ ፡ የምታደርግ ፤ ደግሞ ፡ አንተ ፡ ባለውለታ ፡ ሆንክና ፡ ነው ፡ ከቤቴ ፡ መጥተህ ፡ አሳድሩኝ ፡ የምትለው ፡ በል ፡ አሁን ፡ ቶሎ ፡ ብለህ ፡ ከደጄ ፡ አትሄድም ፤ የመጣኸው ፡ ይህንን ፡ ለፍቼ ፡ ያገኘሁትን ፡ ሀብቴን ፡ ልታጠፋ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ እውነት ፡ አንተ ፡ ማደሪያ ፡ ተቸግረህ ፡ ነውን ፤ ዛሬ ፡ አሳር ፡ ሳይመጣ ፡ ፈጠን ፡ ብለህ ፡ ጥፋልኝ ፡ አለው ። እግዜርም ፡ እያዘነ ፡ እየተከዘ ፡ እኔንስ ፡ አባረሩኝ ፡ እስቲ ፡ አንተን ፡ እሺ ፡ ቢሉህ ፡ ለምናቸው ፡ ብሎ ፡ ክረምትን ፡ ላከው ።

ክረምትም ፡ የዚህ ፡ ቤቶች ፡ እንደ ፡ ምን ፡ ዋላችሁ ፡ የመሸብን ፡ መንገደኞች ፡ ነንና ፡ አሳድሩን ፡ ብሎ ፡ ለመነ ። ያም ፡ ሰው ፡ እንደ ፡ ልማዱ ፡ አንተ ፡ ማነህ ፡ ብሎ ፡ ጠየቀው ። እኔ ፡ ክረምት ፡ ነኝ ፡ ብሎ ፡ ቢመልስለት ፡ ተናደደ ፡ አረረ ፡ ጨሰ ፡ አንተማ ፡ ባንዱ ፡ አገር ፡ የምሕረት ፡ ዝናብ ፡ ታዘንባለህ ፤ ደግሞ ፡ በሌላው ፡ አገር ፡ በረዶና ፡ መብረቅ ፡ እያወረድክ ፡ አዝመራው ፡ ከነቱ ፡ እንደ ፡ ዋለ ፡ ይቀራል ። አንዱን ፡ አገር ፡ በልግ ፡ እንዲሆን ፡ ታደርግና ፡ አንዱን ፡ ደግሞ ፡ ጠብታ ፡ ዝናም ፡ ነፍገህ ፡ ታደርቀዋለህ ፤ ከዚህም ፡ የተነሣ ፡ ሰዉንም ፡ ከብቱንም ፡ በውሃ ፡ ጥም ፡ በረኀብ ፡ ትፈጃለህ ፤ አንተ ፡ ሁሉን ፡ የምታጠቃ ፡ ወንበዴ ፡ ምን ፡ ለማድረግ ፡ ነው ፡ ከደጄ ፡ የመጣኸው ፡ ብሎ ፡ አዋርዶና ፡ ገላምጦ ፡ አባረረው ።



ክረምትም ፡ የደረሰበትን ፡ ዘለፋና ፡ ተግሣጽ ፡ ለጓደኞቹ ፡ ገልጾ ፡ ነገራቸው ። ታዲያ ፡ እዚህ ፡ ተቀምጠን ፡ ጅብ ፡ ይብላን ፤ እስቲ ፡ እባክህ ፡ አንተ ፡ ሂድና ፡ ለምን ፡ ብሎ ፡ ሞትን ፡ አዘዘው ። እሱም ፡ አንተን ፡ ፈጣሪውን ፡ እግዜርን ፡ ሰውነቱን ፡ ከመከራ ፡ የምታድነውን ፡ እንቢ ፡ በማለት ፡ አዋርዶና ፡ ገላምጦ ፡ ያባረረ ፡ አንተንም ፡ ክረምትን ፡ እኽል ፡ የምታበቅልለትን ፡ የሚጠጣውን ፡ ውሃ ፡ የምታፈልቅለትን ፡ የሰደበና ፡ ያባረረ ፡ እኔን ፡ መች ፡ እሺ ፡ ይለኛል ። እንዲያውም ፡ ዘመዶቹን ፡ እናቱን ፡ አባቱን ፡ ልጆቹን ፡ ገድዬ ፡ አሳድረኝ ፡ ብለው ፡ ደብድቦ ፡ ይገድለኛል ፡ ካለ ፡ በኋላ ፡ ትእዛዙ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ስለ ፡ ሆነበት ፡ ተነሥቶ ፡ ሲፈራና ፡ ሲቸር ፡ ሄደና ፡ የዚህ ፡ ቤቶች ፡ እንደ ፡ ምን ፡ ዋላችሁ ፡ አለ ። ሰውየውም ፡ እግዚአብሔር ፡ ይመስገን ፡ እንዴት ፡ ዋልክ ፡ ብሎ ፡ መለሰለት ። ወዳያው ፡ እባካችሁ ፡ የመሸብን ፡ መንገደኞች ፡ አሳድሩን ፡ በማለት ፡ ልመና ፡ አቀረበለት ። አንተ ፡ ማነህ ፡ ቢለውም ፡ እኔ ፡ ሞት ፡ ነኝ ፡ አለው ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ባለቤቱ ፡ ደንግጦ ፡ ከተቀመጠበት ፡ ብድግ ፡ ብሎ ፡ ነምር ፡ ጌታዬ ፡ ከወዴት ፡ መጣህ ፡ ፍርድህ ፡ እንደ ፡ ሚዛን ፡ የተስተካከለ ፡ አንተንማ ፡ ያላሳደርኩ ፡ ማንን ፡ አሳድራለሁ ፤ አንተ ፡ ድሃ ፡ ባለጸጋ ፡ ትንሽ ፡ ትልቅ ፡ ሳትል ፡ ሁሉን ፡ እኩል ፡ የምታደርግ ፡ ያስቀመጥከውን ፡ የማትረሳ ፡ ጌታ ፡ ካንተ ፡ ሌላ ፡ ማንን ፡ ያሳድሯል ፡ ብሎ ፡ በትሩን ፡ ተቀብሎ ፡ ከቤት ፡ አስገብቶ ፡ ምንጣፍ ፡ አንጥፎ ፡ ከመልከም ፡ ድንክ ፡ አልጋ ፡ ላይ ፡ አስቀመጠው ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ሞት ፡ ሁለቱ ፡ ባልደረቦች ፡ ከውጭ ፡ አሉኝ ፡ አለው ። ምነው ፡ ያንተ ፡ ጓደኞች ፡ ሆነው ፡ እስካሁን ፡ ከውጭ ፡ መቀመጣቸው ፡ ቤቱ ፡ ሰፊ ፡ በል ፡ አሁንም ፡ ጥራቸው ፡ ብሎ ፡ በትሕትና ፡ አስታወቀው ። ሞትም ፡ እግዜርንና ፡ ክረምትን ፡ ጠርቶ ፡ ከዚያ ፡ በፊት ፡ እንቢ ፡ ካላቸው ፡ ሰው ፡ ቤት ፡ ካስገባቸው ፡ በኋላ ፡ ሰውየው ፡ ተጨንቆ ፡ ሁሉንም ፡ በታላቅ ፡ ከበሬታ ፡ አሳደራቸው ፡ ይባላል ።

፨ ማናቸውም ፡ ፍጥረት ፡ በእግዚአብሔር ፡ ሥልጣን ፡ ሥር ፡ መሆኑ ፡ ቢታወቅም ፡ ይህ ፡ ምሳሌ ፡ ሰውን ፡ ከሞት ፡ የበለጠ ፡ የሚያስፈራው ፡ እንደ ፡ ሌለ ፡ ያስረዳል ።

# ስለ ፡ አንድ ፡ መሀይምን ፡ መነኰሴ ፡ ጸሎት ።

አንድ ፡ ትምህርት ፡ የሌላቸው ፡ መሀይምን ፡ መነኰሴ ፡ በአንድ ፡ አገር ፡ ውስጥ ፡ ይኖሩ ፡ ነበር ። የዘወትር ፡ ጸሎታቸውም ፡ እንደ ፡ ሥራው ፡ እንደ ፡ ሥራው ፡ ማለት ፡ ነበረ ። በቅራቢያቸውም ፡ እጅግ ፡ ሀብታም ፡ የሆኑ ፡ ሦስት ፡ ልጆች ፡ የወለዱ ፡ በልፍ ፡ ሚስት ፡ ያገኙ ፡ ነበር ። ይህም ፡ በለጸጋ  የድኻን ፡ ርስት ፡ በግፍ ፡ የሚነጥቅ ፡ ከደንብ ፡ የወጣ ፡ የብር ፡ ወለድ ፡ የሚቀበል ፡ ተበዳሪዎቹንም ፡ የሚያስርና ፡ የሚያስጨንቅ ፡ ጨካኝ ፡ ሰው ፡ ነበረ ።

ከዕለታት ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ ወደ ፡ ሞት ፡ የሚያደርስ ፡ ብርቱ ፡ ሕመም ፡ ስላገኘው ፡ ሚስቱ ፡ እኚህን ፡ መነኰሴ ፡ ባሌ ፡ እንዲድን ልኝ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ለምኑልኝ ፡ አለቻቸው ። እሳቸውም ፡ እሺ ፡ ብለው ፡ የዘወትር ፡ ጸሎታቸው ፡ ነውና ፡ እንደ ፡ ሥራው ፡ እንደ ፡ ሥራው ፡ እያሉ ፡ ይጸልዩ ፡ ጀመር ። ወዲያው ፡ የባሏን ፡ ሥራ ፡ ታውቃለችና ፡ ምንድነው ፡ እነደ ፡ ሥራው ፡ የሚሉት ፡ ደኅና ፡ አድርገው ፡ እግዚአብሔርን ፡ ይለምኑለት ፡ እንጂ ፡ አለቻቸው ። መነኰሴው ፡



ምንድነው ፡ እንደ ፡ ሥራው ፡ የምትሉት ፡ ደኅና ፡ አድርገው ፡ እግዚአብሔርን ፡ ይለምኑለት ፡ እንጂ ።

ግን ፡ ሌላ ፡ ጸሎት ፡ አያውቁምና ፡ እንደ ፡ ሥራው ፡ እያሉ ፡ ሲለምኑለት ፡ ሕመሙ ፡ ጠነከረበትና ፡ ሞተ ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ሚስቲቱ ፡ እኚህ ፡ ደንቆሮ ፡ መነኰሴ ፡ እንደ ፡ ሥራው ፡ እንደ ፡ ሥራው ፡ እያሉ ፡ ባሌን ፡ አስገደሉት ፤ ቈይ ፡ እኔም ፡ አደርግላቸዋለሁ ፡ ብላ ፡ ዘዴ ፡



መፈለግ ፡ ያዘች ። አስባም ፡ አልቀረች ፤ ጥቂት ፡ በጥቂት ፡ ምግብ ፡ ትልክላቸው ፡ ጀመር ። ከዕለታት ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ ባሌ ፡ የሞተውን ፡ ሞት ፡ ይሙቱ ፡ ብላ ፡ በስውር ፡ መርዝ ፡ የተጨመረበት ፡ ምግብ ፡ ላከችላቸው ። እሳቸውም ፡ እምጭውን ፡ አሸከር ፡ አቍጣሮዬን ፡ ስጨርስ ፡ እበላዋለሁና ፡ በል ፡ እዚያ ፡ አኑረውና ፡ ሂድ ፡ አሉት ።

ሦስት ፡ የሚቹ ፡ ልጆች ፡ ለአደን ፡ ወደ ፡ በረሓ ፡ ወርደው ፡ ኑሮ ፤ ሲመለሱ ፡ በጣም ፡ ስለ ፡ ራባቸው ፡ የመነኰሴው ፡ ቤት ፡ እመድረሻቸው ፡ ላይ ፡ ነበርና ፡ ፈጥነው ፡ ከሳቸው ፡ ዘንድ ፡ ገብተው ፡ አባታችን ፡ ሆይ ፡ አጥብቆ ፡ ርቦናልና ፡ የሚበላ ፡ ነገር ፡ ያገኙልናልን ፡ ሲሉ ፡ ጠየቋቸው ። እመቤቱ ፡ የላኩልኝ ፡ ድርጎዬ ፡ እንሆ ፡ ተቀምጧልና ፡ እሱን ፡ ተመገቡ ፡ አሏቸው ።



እመቤቴ ፡ የላኩልኝ ፡ ድርጎዬ ፡ እንሆ ፡ ተቀምጧልና ፡ እሱን ፡ ተመገቡ ፡ አሏቸው ፡

ልጆቹም ፡ ተርበው ፡ ስለ ፡ ነበረ ፡ ፈጥነው ፡ወስደው ፡ በሉና ፡ ጥቂት ፡ ሳይቈዩ ፡ ሦስቱም ፡ ሞቱ ። ወዲያው ፡ ተሰሙ ኸና ፡ እናታቸውም ፡ ሰምታ ፡ ሐዘኗ ፡ የመረረ ፡ ለቅሶዋም ፡ የከበደ ፡ ሆነ ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ የልጆቹ ፡ ዘመዶች ፡ መነኰሴውን ፡ ለመግደል ፡ ይጋበዙ ፡ ጀመር ፤ እሷ ፡ ግን ፡ በገዛ ፡ ሥራዬ ፡ ነውና ፡ አትንኳቸው ፡ ብላ ፡ አስጥላ ፡ ከሞት ፡ አተረፈቻቸው ፡ ይባላል ።

፨ ሥራ ፡ ለሠሪው ፡ እሾኽ ፡ ላጣሪው ፡ ነውና ፡ ይህን ፡ የመሰለ ፡ አደጋ ፡ እንዳይደርስብን ፡ በምንሠራው ፡ ሁሉ ፡ ማስተዋልና ፡ መጠንቀቅ ፡ ይገባናል።

እያለች ፡ ስትበሳጭ ፡ ያገኛታል ። ተናዶ ፡ እገርፋለሁ ፡ ብሎ ፡ የነበረውም ፡ እንደ ፡ ገና ፡ ያዝንና ፡ አሁን ፡ እሷን ፡ ያበረርኩ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ልጆቼን ፡ ምን ፡ አደርጋቸዋለሁ ፡ ምን ፡ አባቱ ፡ እነሱ ፡ ከሚበደሉና ፡ የእንጀራ ፡ እናት ፡ ፊት ፡ ከሚገርፋቸው ፡ እኔው ፡ ራሴ ፡ ልጎዳ ፡ "ትሁን ፡ በበ" ፡ ትቀመጥ ፡ ይልና ፡ እንደ ፡ ዋለ ፡ ምሳውን ፡ ሳይበላ ፡ አጣፊኙን ፡ ተከናንቦ ፡ ለበሮቹና ፡ ለላሞቹ ፡ በግርግም ፡ ገለባ ፡ ሊሰጥ ፡ ይወጣል ። ከመሸም ፡ በኋላ ፡ ከብቶቹን ፡ አበረት ፡ አጕሮ ፡ ወደ ፡ ቤቱ ፡ ይገባና ፡ ያገኘውን ፡ አሹቱንም ፡ ምኑንም ፡ በልቶ ፡ እግሩንም ፡ ሳይታጠብ ፡ ከንጭቃው ፡ ይተኛል ። ዘለዓለም ፡ ሕይወቱ ፡ አለፈ ፡ ድረስ ፡ እንደዚሁ ፡ ሲበሳጭና ፡ ሲጎዳ ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ የትዳርን ፡ ፀቅድና ፡ ዘዴ ፡ ሳያይ ፡ ይኖራል ።

ሦስተኛ ፤ እናት ፡ ለምኔ ፤— የዚችም ፡ የትዳሯና ፡ የኑሮዋ ፡ ዘዴ ፡ እንደሚከተለው ፡ ይዘረዘራል ። ቀደም ፡ ብላ ፡ ተነሥታ ፡ ለባሏ ፡ ሙሽት ፡ ለቤ ፡ አሰናድታ ፡ ከመኝታው ፡ ቀስቅሳ ፡ ታቀርባለች ። እሱም ፡ የተዘጋጀለትን ፡ እስቲበላ ፡ በረቱን ፡ ከፍታ ፡ የእርሻ ፡ በሮቹን ፡ ወደ ፡ ጓሮ ፡ አዙራ ፡ ታግጥለታለች ። ሞፈሩን ፡ አንሥቶ ፡ ወደ ፡ እርሻው ፡ ለመሄድ ፡ ሲዘጋጅ ፡ ቶሎ ፡ ብላ ፡ ቀምበሩን ፡ ተሸክማ ፡ ትሸኘዋለች ፤ እንደ ፡ ተመለሰችም ፡ ላሞቹን ፡ ከጥጆቹ ፡ አገናኝታ ፡ ወተቱን ፡ አልባ ፡ ከበቃች ፡ በኋላ ፡ ከብቶቹን ፡ ከመሰማራታቸው ፡ በፊት ፡ ለረኞቹ ፡ ሙሽታቸውን ፡ ትሰጣቸዋለች ።

የምሳ ፡ ሰዓት ፡ ሲደርስ ፡ ደግሞ ፡ የባሏን ፡ ምግብ ፡ በደኅና ፡ አገልግል ፡ ፈትፍታ ፡ የሚጠጣውንም ፡ ጠላ ፡ በቡይት ፡ ይዛ ፡ እርሻው ፡ ድረስ ፡ ትሄዳለች ። እስቲበላ ፡ ድረስም ፡ በሮቹን ፡ ወደ ፡ ወንዝ ፡ ወስዳ ፡ ውሃ ፡ አጠጥታ ፡ ሣር ፡ አግጣ ፡ ታቀርብለታለች ። እሱም ፡ ይህች ፡ መልካም ፡ ሚስቱ ፡ በመጣችለት ፡ ምሳና ፡ መጠጥ ፡ እየተደሰተ ፡ እንደ ፡ ገና ፡ ጠምዶ ፡ ሲያርስ ፡ ያመሻል ። ዕቃዋን ፡ ይዛ ፡ ስትመለስ ፡ በመንገድ ፡ ላይ ፡ የምታገኘውን ፡ ማገዶ ፡ ትለቃቅምና ፡ ወደ ፡ ቤቷ ፡ ገብታ ፡ መቄያውንና ፡ (መክሰስ) ፡ እራቱን ፡ ታሰናዳለታለች ፤ በተረፈውም ፡ ጊዜ ፡ ስፌት ፡ ትሰፋለች ፡ ወይም ፡ ጥጥ ፡ ትሠራለች ።



መሸት ፡ ሲል ፡ ታይናም ፡ ወደ ፡ ውጭ ፡ ወጥታ ፡ ከመንገድ ፡ ላይ ፡ ቀምበሩን ፡ ከባሏ ፡ ተቀብላ ፡ እያጫወተችው ፡ ወደ ፡ ቤት ፡ ትገባለች ። ለበሮቹ ፡ አስቀድማ ፡ ገለባ ፡ አቅርባ ፡ ወዲያው ፡ ለባሏ ፡ መቄያውን ፡ ከቦሬ ፡ ጠላ ፡ ጋራ ፡ ከሰጠችው ፡ በኋላ ፡ የማታ ፡ ሥራዋን ፡ ታሰናዳለች ። ከብቶቹም ፡ ከዱር ፡ ሲገቡ ፡ ከረኞቹ ፡ ተቀብላ ፡ የቀንድ ፡ ከብቱን ፡ ከበረት ፡ በግና ፡ ፍየሉን ፡ ከጋጣ ፡ ታጕራለች ። ባሏንም ፡ ጥቂት ፡ ዕረፍት ፡ እንዳደረገ ፡ አይታ ፡ ከብቶቹን ፡ አውሬ ፡ እንዳይበላቸው ፡ የላላውን ፡ አጥር ፡ ውጣና ፡ አጠባብቅ ፡ ትለዋለች ። እሱም ፡ ደስ ፡ እያለው ፡ በጓሮ ፡ ያስቀመጠውን ፡ አረግ ፡ ወይም ፡ ገመድ ፡ በውሃ ፡ ያርስና ፡ የላላውን ፡ አጥርና ፡ በር ፡ ያጠባብቃል ። ጨርሶ ፡ ወደ ፡ ቤቱ ፡ ሲገባም ፡ ውሃ ፡ በዥስዥስት ፡ ታሞቅና ፡ እግሩን ፡ አጥባ ፡ በቅባት ፡ ታሽለታለች ። እራት ፡ ከበሉም ፡ በኋላ ፡ ቁጡን ፡ እንጥፋ ፡ ታስተኛውና ፡ የቀራትን ፡ ሥራ ፡ ታጠናቅቃለች ። የምትተኛውም ፡ ዐሥር ፡ ልቃቂት ፡ አውጥታ ፡ ስትጨርስ ፡ ነው ።

በእንደዚህ ፡ ያለ ፡ ደስታ ፡ ሲኖሩ ፡ ሳለ ፡ ከዕለታት ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ ወንድዮው ፡ እሑድ ፡ ለት ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ስሞ ፡ ሲመለስ ፡ በጣም ፡ አድርጎ ፡ የሚወደውን ፡ የዱሮ ፡ ጓደኛውን ፡ እመንገድ ፡ ላይ ፡ አገኘና ፡ ዐረፍ ፡ ብለህ ፡ ውሃ ፡ ጠጥተህ ፡ ትሄዳለህና ፡ ወደ ፡ ቤት ፡ እንግባ ፡ ብሎ ፡ ለመነው ። እሱም ፡ ሳይግደረደር ፡ እሺ ፡ አለው ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ምናልባት ፡ የሚበላውና ፡ የሚጠጣው ፡ ይታጣ ፡ ይሆን ፡ እያለ ፡ በልቡ ፡ በመጨነቅ ሲያወጣ ፡ ሲያወርድ ፡ ከቤቱ ፡ ደረሰና ፡ እንግዳውን ፡ እማደያ ፡ አስቀምጦ ፡ ወደ ፡ ሚስቱ ፡ ሄዶ ፡ እኅቴ ፡ ሆይ ፡ ጕድ ፡ ፈላብን ፡ ዛሬ ፤ የዱሮ ፡ ጓደኛዬን ፡ እመንገድ ፡ አግኝቼ ፡ ስግደረደር ፡ ብጋብዘው ፡ እንቢ ፡ ሳይለኝ ፡ ዝም ፡ ብሎ ፡ ተከትሎኝ ፡ መጣ ፡ እንግዲህ ፡ ምን ፡ ላድርገው ፡ ላንቺም ፡ ምንም ፡ አልሰጠሁሽ ፡ አላት ። እሷም ፡ አይዞህ ፡ ሞልቷል ፡ አንተ ፡ ብቻ ፡ ደኅና ፡ ሁን ፡ እንጂ ፡ ግድ ፡ የለህም ፡ ሂድና ፡ እንግዳውን ፡ አጫውተው ፡ ብላ ፡ ወዲያው ፡ ድስቷን ፡ ጥዳ ፡ ወጡን ፡ አድርሳ ፡ አፍ ፡ ማሟሻ ፡ ሰጠቻቸው ። በየጃቸውም ፡ አንዳንድ ፡ ሸክና ፡ ጠላ ፡ አሲያዘቻቸው ፤ ቡናም ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ወቅጣ ፡ ስለምታስቀምጥ ፡ እነሱ ፡ እስቲበሉ ፡ ውሃውን ፡ ጥዳ ፡ አፍልታ ፡ ወዲያው ፡ አመጣች ። ቀጥሎም ፡ አዲስ ፡ የተመረገ ፡ ጠላ ፡ ስለ ፡ ነበራት ፤ በዶጮ ፡ ሞልታ ፡ በሉ ፡ እየተጫወታችሁ ፡ ጠጡ ፡ ብላ ፡ አቀረበችላቸው ። ወደ ፡ ደጅም ፡ ወጣ ፡ አለችና ፡ ባሏን ፡ ጠቅሳ ፡ ጠርታ ፡ ለጓደኛህ ፡ አንድ ፡ በግ ፡ እረድለት ፡ ደስ ፡ ብሎት ፡ ይደር ፡ አለችው ። እሱም ፡ እሺ ፡ ብሎ ፡ ቃሏን ፡ ተቀብሎ ፡ ከበጎቹ ፡ ማኽል ፡ ደኅናውን ፡ ሙክት ፡ መርጦ ፡ አረደ ። ባለቤቲቱም ፡ ቶሎ ፡ ብላ ፡ አፋጥና ፡ ዱለ

በፍጥነት ፡ ድረስ ፡ ብለውሃልና ፡ ተነሣ ፡ ታጠቅና ፡ እንሂድ ፡ አለው ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ልጁ ፡ ዛሬስ ፡ በርግጡ ፡ ሕይወቴ ፡ የሚያልፍበት ፡ ዘመን ፡ ደረሰ ፤ እንግዲህ ፡ ከቶ ፡ መዳን ፡ የለኝም ፡ ብሎ ፡ ተስፋውን ፡ ፈጽሞ ፡ ቈረጠ ። ያች ፡ ተኵላ ፡ እንኳ ፡ ከሞት ፡ እንዳታድነኝ ፡ ስለ ፡ በጎ ፡ ሥራዋ ፡ በፊት ፡ በጦር ፡ ሳትኳት ፤ በሁለተኛው ፡ ጊዜ ፡ ደግሞ ፡ ጕድጓዷን ፡ ጭድ ፡ ጠቅጥቄ ፡ በጭስ ፡ አፍኜ ፡ ገደልኳት ፤ ከእንግዲህ ፡ ወዲህ ፡ ሞት ፡ አልቀረልኝም ፡ እያለ ፡ ማልቀስ ፡ ያዘ ። ትእዛዝ ፡ ነውና ፡ መሄድ ፡ ግድ ፡ ሆኖበት ፡ ፊቱን ፡ አጥቍሮ ፡ አደምኖ ፡ እያነባ ፡ ሲጓዝ ፡ ሳለ ፤ አሁንም ፡ ያችው ፡ ተኵላ ፡ ከመንገድ ፡ ዳር ፡ ተቀምጣ ፡ አገኛትና ፡ እንደ ፡ ቀድሞው ፡ ሁሉ ፡ ምን ፡ ሆንክ ፡ ብላ ፡ ብትጠይቀው ፡ ሳትቃጠል ፡ በመዳኗ ፡ በጣም ፡ ተገርሞ ፡ ስለ ፡ ራሱ ፡ ሁኔታ ፡ ያለበትን ፡ ሥጋት ፡ ነገራት ። ተኵላይቱም ፡ አይዞህ ፡ አትሞትም ፡ ዘንድሮ ፡ የጥጋብ ፡ ዘመን ፡ ነው ፡ ብለህ ፡ ንገረው ፡ ካለች ፡ በኋላ ፡ በመምጫህ ፡ ሰዓት ፡ ሥጋ ፡ ይዘህልኝ ፡ ና ፡ ስትል ፡ አደራ ፡ ጭምር ፡ አሳሰበችው ።

በጎውን ፡ ውለታ ፡ በክፋት ፡ የሚመልሰውም ፡ ወጣት ፡ ሄዶ ፡ የጥጋብ ፡ ዘመን ፡ ነው ፡ ሲል ፡ ያለድንጋጤና ፡ ማፈር ፡ ከንጉሡ ፡ ዙፋን ፡ ፊት ፡ ቀርቦ ፡ በገሀድ ፡ ተናገረ ። ንጉሡም ፡ የጥጋብ ፡ ዘመን ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ በማብሠሩ ፡ ይኸንኑ ፡ ሕዝቡ ፡ በሙሉ ፡ እንዲሰማው ፡ መለከት ፡ አስነፋ ፤ ነጋሪትም ፡ አስጐሸመ ። ሰራዊቱ ፡ በተነገረው ፡ ትንቢት ፡ እንዲደሰት ፡ ከደረገም ፡ በኋላ ፡ ልጁን ፡ የሚያስፈልገውን ፡ ክብር ፡ ሰጥቶ ፡ ሸልሞ ፡ መሳፍንቱን ፡ መኳንንቱን ፡ የሀገር ፡ ሽማግሎቹን ፡ በሙሉ ፡ ሰብስቦ ፡ ደስታ ፡ የተመላበት ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ግብር ፡ አደረገ ። ወጣቱም ፡ ግብር ፡ ምላሽ ፡ ሲሆን ፡ ለተደረገለት ፡ ክብር ፡ መሬት ፡ ስሞ ፡ ተሰናብቶ ፡ ወደ ፡ ቤቱ ፡ ለመሄድ ፡ ተነሣ ።

በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ያች ፡ ተኵላ ፡ ዘለዓለም ፡ ከጕድ ፡ ከመከራ ፡ ታወጣኛለች ፡ እኔ ፡ ግን ፡ ዘወትር ፡ ክፋትና ፡ ተንኰል ፡ ከማሰብ ፡ በቀር ፡ የሠራሁላት ፡ በጎ ፡ ሥራ ፡ የለም ። እስቲ ፡ አሁን ፡ እንኳ ፡ ያንን ፡ ያለችኝን ፡ ልውሰድላት ፡ ብሎ ፡ ሥጋውን ፡ ይዞ ፡ ሄደና ፡ ይኸው ፡ የጠየቅሽኝን ፡ ይዤልሽ ፡ መጥቻለሁ ፤ ነገር ፡ ግን ፡ አንቺ ፡ ለኔ ፡ ዘወትር ፡ በጎ ፡ ሥራ ፡ ስትሠሪልኝ ፡ ሳለ ፡ እኔ ፡ ያንቺን ፡ መልካሙን ፡ ሥራ ፡ በክፋት ፡ መልሼ ፡ በፊተኛው ፡ ጊዜ ፡ በጦር ፡ ልገድልሽ ፡ ብወረውር ፡ በቅንነትሽ ፡ አምላክ ፡ ከመሞት ፡ አዳነሽ ፤ ሁለተኛ ፡ ደግሞ ፡ የፊቱ ፡ ጥፋቱና ፡ በደሌ ፡ አልበቃ ፡ ብሎኝ ፡ ጕሬሽን ፡ በጭድ ፡ ጠቅ



ጥቄ ፡ እሳትን ፡ ያኽል ፡ በለጋራ ፡ ብለቅብሽም ፡ ከደግነትሽና ፡ ከእውነተኛነትሽ ፡ የተነሣ ፡ ሳትቃጠይ ፡ ዳንሽ ፤ ይህ ፡ ሁሉ ፡ ሊሆን ፡ የቻለው ፡ ቅን ፡ ልቡና ፡ ስላለሽ ፡ ነውና ፡ አሁንም ፡ ባለፈው ፡ የበደልኩሽን ፡ በደል ፡ ሁሉ ፡ ይቅር ፡ ብለሽ ፡ ዛሬ ፡ ያመጣሁልሽን ፡ ሥጋ ፡ ተቀበይኝ ፡ አላት ።



ባለፈው ፡ የበደልኩሽን ፡ በደል ፡ ሁሉ ፡ ይቅር ፡ ብለሽ ፡ ዛሬ ፡ ያመጣሁልሽን ፡ ሥጋ ፡ ተቀበዪኝ ፡ አላት ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ሰማህ ፡ ወንድሜ ፡ ነቃ ፡ ብለህ ፡ አዳምጠኝ ፡ ልንገርህ ። በፊተኛው ፡ ጊዜ ፡ ጦር ፡ የወረወርክብኝ ፡ ዘመኑ ፡ የጦርነት ፡ ዘመን ፡ ስለ ፡ ነበረ ፡ ነው ፤ በሁለተኛው ፡ ጊዜ ፡ ደግሞ ፡ በጭድ ፡ አድርገህ ፡ እሳት ፡ የለቀቅህብኝ ፡ የበሽታ ፡ ዘመን ፡ በመሆኑ ፡ ነው ። አሁን ፡ ግን ፡ በሦስተኛው ፡ ጊዜ ፡ ቃሌን ፡ ፈጽመህ ፡ ሥጋውን ፡ ይዘህልኝ ፡ መምጣትህ ፡ ዘመኑ ፡ ጥጋብ ፡ በመሆኑ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ እውነት ፡ አንተ ፡ ከቀድሞ ፡ ክፋትህ ፡ ተመልሰህና ፡ ለኔ ፡ አዝነህ ፡ አይደለም ። ከዚህ ፡ ቀድሞም ፡ የበደለኝ ፡ ዘመን ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ አንተ ፡ አይደለህም ፤ አሁንም ፡ የሰጠኝ ፡ ዘመኑ ፡ እንጂ ፡ አንተ ፡ አይደለህም ፤ የሚሰጥም ፡ የሚነሣም ፡ ዘመን ፡ ነው ፤ የሰው ፡ ደግነቱም ፡ ክፋቱም ፡ እንደ ፡ ዘመኑና ፡ እንደ ፡ ጊዜው ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ አንተ ፡ ጥፋት ፡ ወይም ፡ በደል ፡ በኔ ፡ ላይ ፡ አልሠራህም ፡ ብላ ፡ የጊዜን ፡ ደግነትና ፡ ክፋት ፡ ትርጓሜ ፡ ገልጣ ፡ ነገረችው ፡ ይባላል ።

❊ የተወደዳችሁ ፡ ወጣቶች ፡ ሆይ ፡ ከናት ፡ ቀን ፡ ይሻላል ፡ የተባለው ፡ ያባቶች ፡ ተረት ፡ ፍሬ ፡ ያለው ፡ በጠነከረ ፡ መሠረት ፡ ላይ ፡ የተቋቋመ ፡ መሆኑን ፡ አስተውሉ ።

# ስለ ፡ ሁለት ፡ ጓደኞች ።

ሁለት ፡ ከልብ ፡ የሚተማመኑ ፡ ባልንጀሮች ፡ በየጊዜው ፡ ይገጥማቸው ፡ የነበረውን ፡ ችግር ፡ ሁሉ ፡ በመረዳዳት ፡ እያቃለሉ ፡ ትዳር ፡ ይዘው ፡ ይኖሩ ፡ ነበር ። ይልቁንም ፡ አንደኛው ፡ የጓደኛ ፡ ፍቅር ፡ በጣም ፡ ይጸናበት ፡ ስለ ፡ ነበረ ፡ ወዳጁ ፡ የሚጠይቀውን ፡ ሁሉ ፡ ያላንድ ፡ ቅሬታ ፡ ይፈቅድለት ፡ ነበር ። ነገር ፡ ግን ፡ ሁለተኛው ፡ ይሉኝታ ፡ ቢስ ፡ በመሆኑ ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ ያገር ፡ ሽማግሌዎች ፡ ሰብስቦና ፡ አበቶቼ ፡ ሆይ ፡ ዛሬ ፡ የማስቸግራችሁ ፡ ይህ ፡ ባልንጀራዬ ፡ ያገባት ፡ ሴት ፡ በውበት ፡ በደም ግባት ፡ በቅርጽና ፡ በረማመድ ፡ ያማረች ፡ ከመሆኗም ፡ በላይ ፡ ያይኗ ፡ አገላለጥና ፡ አከዳደን ፡ ልቤን ፡ ስለ ፡ ነደፈው ፡ ለወንድሜ ፡ ነግራችሁ ፡ ይህችን ፡ ውብ ፡ ሴት ፡ እንዳገኝ ፡ አድርጉልኝ ፡ ሲል ፡ ልመናውን ፡ አቀረበላቸው ።

ሽማግሌዎችም ፡ ይህ ፡ ሀይነት ፡ ሐሳብ ፡ ከዚህ ፡ በፊት ፡ ተሰምቶ ፡ ያልታወቀ ፡ በመሆኑና ፡ እንግዳ ፡ ነገር ፡ ስለ ፡ ሆነባቸው ፡ ተደንቀው ፡ እኛ ፡ ባልና ፡ ሚስት ፡ እንዲስማሙ ፡ እናደርጋለን ፡ እንጂ ፡ እንዲለያዩ ፡ እንሠራም ፡ ብለው ፡ ተቈጡ ። እሱ ፡ ግን ፡ ንግግሩን ፡ በማለዘብና ፡ በማለስለስ ፡ ሄዳችሁ ፡ እባክህ ፡ ሚስትህን ፡ ለእገሌ ፡ ለኛ ፡ ስትል ፡ ስጥልን ፡ በሉት ፡ እንጂ ፡ ወንድሜ ፡ የለመንኩትን ፡ እንደማይነሣኝ ፡ ዐውቃለሁ ፡ ሲል ፡ ደግሞ ፡ አስጨንቆ ፡ ጠየቃቸው ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ሽማግሌዎቹ ፡ እንደ ፡ ምንም ፡ ሲፈሩ ፡ ሲቸሩ ፡ ሄደው ፡ ከሰውየው ፡ አጥር ፡ ግቢ ፡ ሲደርሱ ፡ ሁለቱ ፡ አንተ ፡ ተናገር ፡ አንተ ፡ ተናገር ፡ በማለት ፡ እምባጓሮ ፡ እንሥተው ፡ ተማተው ፡ ቈስለው ፡ ተመለሱ ። ይሁን ፡ እንጂ ፡ የተረፉት ፡ አማላጆች ፡ በድፍረት ፡ ወደ ፡ ቤት ፡ ገብተው ፡ ምንም ፡ እንኳ ፡ ነገሩ ፡ አሰቃቂ ፡ ቢሆን ፡ ዛሬ ፡ አንተን ፡ ወንድማችንን ፡ የምናስቸግርህ ፡ ለዚህ ፡ ለአብሮ ፡ አደግ ፡ ጓደኛህ ፡ ሚስትህን ፡ እንድትለቅለት ፡ ነው ፡ በማለት ፡ የመጡበትን ፡ ጕዳይ ፡ ዘርዝረው ፡ ገለጹለት ። ይሁን ፡ እሺ ፡ ለናንተ ፡ ስል ፡ ሚስቴን ፡ ለወንድሜ ፡ እተዋለሁ ፤ ነገር ፡ ግን ፡ ለኔ ፡ ደግሞ ፡ ከናንተ ፡ አንዳችሁ ፡ ሚስታችሁን ፡ እንድትለቁልኝ ፡ እለምናችኋለሁ ፡ ብሎ ፡ መልስ ፡ ሰጣቸው ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ሽማግሌዎቹ ፡ በሚስት ፡ የለም ፡ ዋዛ ፡ ብለው ፡ ከቤት ፡ ወጥተው ፡ ሄዱ ፡ ይባላል ።



፨ ስለዚህ ፡ እነሱ ፡ ራሳቸው ፡ ሊያደርጉት ፡ የማይችሉትንና ፡ የማይፈቅዱትን ፡ ነገር ፡ እንዲፈጽሙላቸው ፡ ሌሎችን ፡ የሚጠይቁ ፡ ሽማግሌዎች ፡ ይህንን ፡ የመሰለ ፡ ቅሌትና ፡ ትዝብት ፡ እንዳይተርፉ ፡ መጠንቀቅ ፡ እንዳለባቸው ፡ ይወቁ ።

# አንድ ፡ አሮጌ ፡ ውሻና ፡ ቀበሮ ።

ዕድሜውን ፡ ሙሉ ፡ በቅንነትና ፡ በታማኝነት ፡ ለጌታው ፡ ሲያገለግል ፡ የኖረ ፡ አንድ ፡ አሮጌ ፡ ውሻ ፡ ጊዜ ፡ ሞቱ ፡ ሲደርስ ፡ ካቅሙ ፡ ማነስ ፡ የተነሣ ፡ የዘበኝነት ፡ ሥራውን ፡ እርግፍ ፡ አድርጎ ፡ ትቶ ፡ በምግብ ፡ ሰዓት ፡ ብቻ ፡ ዐይኑን ፡ እያንከራተተ ፡ ቤት ፡ ለቤት ፡ መልከስከስ ፡ ዠመረ ።

በዚህ ፡ ጊዜ ፡ አሳዳሪው ፡ የሆኑት ፡ ጌቶቹ ፡ በከንቱ ፡ እሱን ፡ ከምንቀልብ ፡ ብንገድለውና ፡ በምትኩ ፡ ቡችላ ፡ ብናሳድግ ፡ የተሻለ ፡ ነው ፡ እያሉ ፡ ሲመካከሩ ፡ በመስማቱ ፡ እጅግ ፡ አዘንና ፡ ወደ ፡ መናፈሻ ፡ ወጥቶ ፡ የዱሮ ፡ አገልግሎቱን ፡ እያስታወሰ ፡ ማልቀስ ፡ ያዘ ። እንዳጋጣሚ ፡ ቀበሮ ፡ እግረ ፡ መንገዷን ፡ በዚያው ፡ በኩል ፡ ታልፍ ፡ ነበርና ፤ የውሻው ፡ ሁናቴ ፡ ስላሳዘናት ፡ ጠጋ ፡ ብላ ፡ በምን ፡ ምክንያት ፡ እንዳዘነና ፡ እንደ ፡ ተከዘ ፡ ጠየቀችው ። እሱም ፡ ጌቶቹ ፡ የሞት ፡ ሴራ ፡ እንደ ፡ ቋጠሩበት ፡ ነገራት ።

ቀበሮዋ ፡ በነገሩ ፡ በጣም ፡ ተደነቀችና ፡ አቶ ፡ ውሻን ፡ ምንም ፡ እንኳ ፡ ባንተና ፡ በኔ ፡ ዘር ፡ መካከል ፡ ቂም ፡ በቀል ፡ ቢኖር ፡ በስተርጅና ፡ መጠቃትህ ፡ በጣም ፡ አሳዝኖኛልና ፡ ከሞት ፡ የምትድንበትን ፡ ዘዴ ፡ ልምከርህ ፡ አለችው ። አሮጌውም ፡ ዘበኛ ፡ እንዲህ ፡ ያለ ፡ ተስፋ ፡ በማግኘቱ ፡ ከሐዘኑ ፡ ተጽናና ፤ በእንዴት ፡ ያለ ፡ ጥበብ ፡ ከዚህ ፡ አደጋ ፡ ልድን ፡ እችላለሁ ፡ ሲል ፡ ጠየቃት ።

ከጌቶችህ ፡ ምሕረት ፡ ለማግኘት ፡ ብትፈልግ ፡ ነገ ፡ ጧት ፡ ባለቤቶቹ ፡ ወደ ፡ ውጭ ፡ በሚወጡበት ፡ ሰዓት ፡ እኔ ፡ ወደ ፡ ቤት ፡ ልምጣና ፡ ሕፃኑን ፡ ልጃቸውን ፡ ልውሰደው ፤ በዚያ ፡ ጊዜ ፡ አንተ ፡ እንደ ፡ ምንም ፡ ብለህ ፡ እየተጐተትህ ፡ ተከተለኝ ፤ አሳዳሪዎችህ ፡ ወሮታህን ፡

እነሱም ፡ ምንም ፡ ለጊዜው ፡ ቢደነግጡ ፡ የወደቀባቸውን ፡ ተነሥተው ፡ ቢያዩት ፡ ወርቅ ፡ የተመላበት ፡ ከረጢት ፡ ሆኖ ፡ አገኙት ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ይህ ፡ በሽተኛ ፡ ሰው ፡ ለሚስቱ ፡ እኔ ፡ ያልኩሽ ፡ ነገር ፡ ደረሰ ፡ ቀን ፡ ላምጣው ፡ ብትዪኝ ፡ ለኛ ፡ ካለው ፡ እግዚአብሔር ፡ ያመጣዋል ፡ እንዳልኩሽ ፡ ይኸው ፡ አምላክ ፡ በጃችን ፡ ሰጠን ፡ አለና ፡ በእምነት ፡ ላይ ፡ ያለውን ፡ ትልቅ ፡ ኃይል ፡ አስረዳት ።

ከዚህም ፡ በኋላ ፡ በወርቁ ፡ መድኀኒት ፡ ገዝቶ ፡ ከሕመሙ ፡ ተፈውሶ ፡ ድኖ ፡ በዓለም ፡ በደስታ ፡ ከነባለቤቱ ፡ ፈጣሪውን ፡ እያመሰገነ ፡ ትዳሩን ፡ አደርጅቶ ፡ ኖረ ፡ ይባላል ።

፨ እግዚአብሔር ፡ ላንዱ ፡ ያዘዘለትን ፡ ሌላው ፡ ሊወስደው ፡ አይችልም ፡ ከዚህ ፡ ላይም ፡ እምነት ፡ ተራራ ፡ ይፈነቅላል ፡ ባሕር ፡ ይከፍላል ፡ የተባለውን ፡ አለመዘንጋት ፡ ይገባል ።

# አንድ ፡ ቀላዋጭ ፡ ሰው ።

ዕድሜ ፡ ልኩን ፡ በቅልውጥ ፡ የሚኖር ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ነበር ። እሱም ፡ ሁል ፡ ጊዜ ፡ በካባቢው ፡ ያሉት ፡ ሰዎች ፡ እኽል ፡ ውሃ ፡ የሚቀምሱበትን ፡ ሰዓት ፡ እየጠበቀ ፡ በየተራ ፡ ጎረ ፡ ቤቶቹን ፡ ያስቸግር ፡ ነበር ።

ነገር ፡ ግን ፡ አንድ ፡ ዓመት ፡ በሀገሩ ፡ ውስጥ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ የእኽል ፡ ችግር ፡ ስለ ፡ ገባ ፡ እንኳን ፡ ለውጭ ፡ ሰው ፡ ለመስጠት ፡ ይቅርና ፡ ለራስም ፡ የሚበላ ፡ ለማግኘት ፡ አዳጋች ፡ ሆነ ። ።

ስለዚህም ፡ ጎረ ፡ ቤቶቹ ፡ ሁሉ ፡ ስለ ፡ ሰለቹትና ፡ በማጣታቸውም ፡ ጭምር ፡ ስለ ፡ ተመረሩት ፡ ከውጭ ፡ የሰላምታ ፡ ድምፅ ፡ ባሰሙት ፡ ጊዜ ፡



ቶሎ ፡ ብለው ፡ ገበታቸውን ፡ ያነሡና ፡ አፋቸውን ፡ ጠራርገው ፡ ነወር ፡ አቶ ፡ እገሌ ፡ ምሳችንን ፡ ከበላን ፡ በኋላ ፡ መጣህ ፡ ምነው ፡ ትንሽ ፡ ቀደም ፡ ባልክ ፡ ኖሮ ፡ ደኅና ፡ ነበር ፡ እያሉ ፡ የማያበሉት ፡ ሆኑ ።

በእንደዚህም ፡ ያለ ፡ ሁኔታ ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ሲቸገር ፡ ከቈየ ፡ በኋላ ፡ ከዕለታት ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ ከንደኛው ፡ ጎረ ፡ ቤት ፡ ገንፎ ፡ ተገንፍቶ ፡ ሲቀርብ ፡ ይህ ፡ ቀላዋጭ ፡ ድንገት ፡ ከበር ፡ ላይ ፡ ከተፍ ፡ አለ ። ባለቤትየውም ፡ ቶሎ ፡ ብሎ ፡ ምግብ ፡ ያለበትን ፡ ጣባ ፡ አንሥቶ ፡ ከጕያው ፡ ውስጥ ፡ ሸሽገና ፡ ጋቢውን ፡ ተከናንቦ ፡ ተመለከተው ። ይሁን ፡ እንጂ ፡ በእንፋሎቱ ፡ መውጣት ፡ እንግዳው ፡ ሰውዬ ፡ በባለቤቱ ፡ ጕያ ፡ ውስጥ ፡ ገንፎ ፡ መኖሩን ፡ ለማወቅ ፡ ችሏል ። ስለዚህም ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ ጨዋታ ፡ አመጣ ። ዛሬ ፡ ካቶ ፡ እገሌ ፡ ቤት ፡ ብሄድ ፡ ገንፎ ፡ አስገንፍቶ ፡ ሲበላ ፡ ደረስኩ ፡ ዳሩ ፡ ግን ፡ ሊነፍገኝ ፡ ፈልጎ ፡ ኖሮ ፡ እንዳላይበት ፡ ከጕያው ፡ አግብቶ ፡ ደበቀው ፡ እኔም ፡ ምሥጢሩ ፡ ስለ ፡ ገባኝ ፡ ቀስ ፡ አልሁና ፡ ጋቢውን ፡ ወደ ፡ ላይ ፡ ገለጥ ፡ ባደርገው ፡ ያን ፡ ገንፎ ፡ የተመላውን ፡ ጣባ ፡ ቅቤ ፡ እንዳረገዘ ፡ አገኘሁት ፡ አለና ፡ እንደ ፡ ማሳየት ፡ ዐይነት ፡ አድርጎ ፡ የሰውዬውን ፡ ጋቢ ፡ ይዞ ፡ ወደ ፡ ላይ ፡ አለው ፡ ከዚህም ፡ የተነሣ ፡ ጣባው ፡ ታየበት ።



የሰውዬውን ፡ ጋቢ ፡ ይዞ ፡ ወደ ፡ ላይ ፡ አለው ፡ ከዚህም ፡ የተነሣ ፡ ጣባው ፡ ታየበት ።

በእንደዚህ ፡ ያለ ፡ ዘዴ ፡ እረ ፡ አንተም ፡ ይዘሃልና ፡ ብሎ ፡ ገንፎውን ፡ በልቶ ፡ ሄደ ፡ ይባላል ።

፨ ተረት ፡ አጕንብሶ ፡ በላን ፡ ተኝተህ ፡ ቀላውጠው ።

# የታማኝ ፡ ወዳጆች ፡ መከዳዳት ።

ባንድ ፡ አገር ፡ የሚተማመኑ ፡ ሁለት ፡ ሰዎች ፡ ነበሩ ። ከነዚህም ፡ አንደኛው ፡ በሀብቱ ፡ የገነነ ፡ በሽምግልናው ፡ የተከበረ ፡ ሲሆን ፡ ሁለተኛው ፡ ደግሞ ፡ እየሠራ ፡ ከሚያፈራው ፡ ከዕለት ፡ ምግቡ ፡ ከመጣ ፡ ልብሱ ፡ የሚተርፈውን ፡ ገንዘቡን ፡ እየወሰደ ፡ በዱሩ ፡ ስም ፡ አኑርልኝ ፡ እያለ ፡ ለባለጸጋው ፡ የሚሰጥ ፡ ነበር ። ያም ፡ ታማኝ ፡ መሰዩ ፡ ሽማግሌ ፡ ያደራውን ፡ ገንዘብ ፡ እየተቀበለ ፡ ሲያስቀምጥለት ፡ ቈይቶ ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ ባለ ገንዘቡ ፡ ለዕለት ፡ ችግሩ ፡ ከኖረው ፡ ሒሳብ ፡ ላይ ፡ ጥቂት ፡ እንዲሰጠው ፡ ቢጠይቀው ፡ ምን ፡ ሰጠኸኝና ፡ ትጠይቀኛለህ ፡ አላየሁም ፡ ብሎ ፡ ጨርሶ ፡ ከደው ፤ እየተመላለሰ ፡ በማሳዘን ፡ ቢለምነውም ፡ አላዘነለትም ፡ አልራራለትም ።

ቍርጡንም ፡ ካወቀ ፡ በኋላ ፡ ላገሩ ፡ ዳኛ ፡ ክስ ፡ ለማቅረብ ፡ ሄዶ ፡ አመለከተ ፡ ዳኛውም ፡ ስትሰጠው ፡ ያየህ ፡ ምስክር ፡ የሚሆን ፡ ሰው ፡ አለህን ፡ ብሎ ፡ ቢጠይቀው ፡ ከኔና ፡ ከሱ ፡ በቀር ፡ ማንም ፡ ሰው ፡ አልነበረም ፡ አለው ። እንግዲያስ ፡ እኔ ፡ እጠይቅልሃለሁና ፡ ከሦስት ፡ ቀን ፡ በኋላ ፡ ተመልሰህ ፡ እንድትመጣ ፡ ብሎ ፡ አስታወቀው ።

ብልኁ ፡ ዳኛ ፡ እደራ ፡ አስቀማጩን ፡ ሰው ፡ ጠርቶ ፡ አሁን ፡ ያስጠራሁህ ፡ እኔ ፡ በድንገት ፡ ከዚህ ፡ አገር ፡ ከሹመቱ ፡ ተሽሬ ፡ መሄዴ ፡ ነው ፤ ብጠይቅም ፡ በስጠይቅም ፡ ታማኝ ፡ ሽማግሌ ፡ በገር ፡ ያለኸው ፡ አንተ ፡ መሆንህን ፡ሰማሁ ፡ ስለዚህ ፡ ዕቃዬንና ፡ ያለኝን ፡ ገንዘቤን ፡ በሙሉ ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ እንዶቼ ፡ ለመሄድ ፡ ስለማይቻለኝ ፡ አንተ ፡ ዘንድ ፡ እንድታስቀምጥልኝና ፡ በየጊዜው ፡ ሰው ፡ ስልክ ፡ እንድትሰጥልኝ ፡ እለምንሃለሁ ፡ አለው ።

ሽማግሌውም ፡ እንግዲህ ፡ ይህ ፡ ያገር ፡ ዳኛ ፡ ትልቅ ፡ ሰው ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ በደራ ፡ የሚያስቀምጠው ፡ ገንዘብ ፡ በብዙ ፡ ሺ ፡ የሚቈጠር ፡ ዕቃውም ፡ ከይነቱ ፡ ብዛት ፡ ጋራ ፡ የበረከተ ፡ ይሆናልና ፡ ይኸን ፡ ተቀብዬ ፡ አላየሁም ፡ ብዬ ፡ በለሀብት ፡ ባለገንዘብ ፡ እሆናለሁ ፡ ብሎ ፡ ደስ ፡ አለውና ፡ ለዳኛው ፡ እሺ ፡ ጌታዬ ፡ ሲል ፡ መልስ ፡ ሰጠው ።



ከሦስት ፡ ቀንም ፡ በኋላ ፡ ያ ፡ ባለገንዘብ ፡ ለዳኛው ፡ በቀጠሮዬ ፡ መጥቻለሁ ፡ ብሎ ፡ አመለከተው ። እንግዲህ ፡ ሂድና ፡ አንዳችም ፡ ነገር ፡ ሳትጨምር ፡ ባገሩ ፡ ዳኛ ፡ ልከስህ ፡ ነውና ፡ ገንዘቤን ፡ ስጠኝ ፡ በለው ፤ በዚያም ፡ ጊዜ ፡ ገንዘብህን ፡ በሙሉ ፡ አንድም ፡ ሳያስቀር ፡ ጨርሶ ፡ ይሰጥሃል ፡ አለው ።

እንደ ፡ ተባለውም ፡ ሁሉ ፡ ሄዶ ፡ ቢጠይቀው ፡ ይህን ፡ አልሰጥም ፡ ያልኩት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ለዳኛው ፡ ሲነግረው ፡ ከሓዲነቴን ፡ ያውቅብኝና ፡ የሱን ፡ ብዙውን ፡ ገንዘብና ፡ ዕቃ ፡ ያስቀርብኛል ፡ ሲል ፡ ገንዘቡን ፡ በሙሉ ፡ አውጥቶ ፡ ሰጠው ፡ ይባላል ።



ከሓዲነቴን ፡ ያውቅብኝና ፡ የሱን ፡ ብዙውን ፡ ገንዘብና ፡ ዕቃ ፡ ያስቀርብኛል ፡ ሲል ፡ ገንዘቡን ፡ በሙሉ ፡ አውጥቶ ፡ ሰጠው ።

፨ በጥቂት ፡ ያልታመነ ፡ ለብዙ ፡ አይታመንም ።

ብልህ ፡ ዳኛ ፡ የሕዝብ ፡ እረኛ ።

እነሱም ፡ ምን ፡ መዓት ፡ ወረደብን ፡ በማለት ፡ ቍስለኛውን ፡ አንበሳ ፡ ተከትለው ፡ ሸሹ ፤ ሰውየውም ፡ በእንደዚህ ፡ ያለ ፡ ዘዴ ፡ ከሞት ፡ ዳነ ፡ ይባላል ።

አራዊት ፡ ምንም ፡ ግዙፍ ፡ ወይም ፡ ኃይለኛ ፡ ወይም ፡ ደግሞ አስፈሪ ፡ ቢሆኑ ፡ የሰው ፡ ልጅ ፡ በተፈጥሮ ፡ ባገኘው ፡ ዕውቀቱ ፡ ማናቸውንም ፡ በጥበቡና ፡ በብልኀቱ ፡ ያሸንፋቸዋል ።

፨ አንዳንድ ፡ ጊዜም ፡ ጠላት ፡ ከመሣሪያ ፡ ይልቅ ፡ በመንፈስ ፡ ኃይል ፡ የበለጠ ፡ ይጠቃል ።

—ደፋርና ፡ ጢስ ፡ መውጫ ፡ አያጣም ፤

—ጦር ፡ ከፊታው ፡ ወሬ ፡ የፊታው ፡ ይበልጣል ፤

—ከትልቅ ፡ ጉልበት ፡ ትንሽ ፡ ብልኀት ፡ እየተባለ ፡ የሚተረተውም ፡ ይኸንን ፡ የመሳሰለ ፡ ነገር ፡ ባጋጠመ ፡ ጊዜ ፡ መሆኑን ፡ መገንዘብ ፡ ይገባል ።

# ጠበል ፡ የሄደች ፡ ፍየል ።

አንዲት ፡ ፍየል ፡ አያሌ ፡ ዘመን ፡ ብቻዋን ፡ ትኖር ፡ ነበር ። ከብቸኝነቷም ፡ ብዛት ፡ የተነሣ ፡ ብዙ ፡ ነገር ፡ በማሰብ ፡ በመጨነቅና ፡ በመሥጋት ፡ አካሏ ፡ እየከሰሰ ፤ ዐይኗዋ ፡ እየደከመ ፡ ስለ ፡ ሄደ ፡ ሕመም ፡ በጣም ፡ አድርጎ ፡ ያጠቃት ፡ ዠመር ። ከሚያውቃያትም ፡ ደዌ ፡ ለመዳን ፡ ወደ ፡ ጠበል ፡ ለመሄድ ፡ ቍርጥ ፡ ሐሳብ ፡ አደረገች ። ጕዞዋንም ፡ ዠምራ ፡ ሳለች ፡ በምትሰነብትበት ፡ ጊዜ ፡ ሁሉ ፡ አንድ ፡ ጓደኛ ፡ ማግኘት ፡ አስፈላጊዋ ፡ መሆኑ ፡ ተሰማትና ፡ አንዲት ፡ ጤናዋ ፡ የተሰናከለ ፡ የምታውቃትን ፡ በግ ፡ ይዛ ፡ ለመሄድ ፡ ተመኘች ። እግዚአብሔር ፡ የለመኑትን ፡ የማያስቀር ፡ በመሆኑ ፤ ጥቂት ፡ እንደ ፡ ሄደች ፡ በጊቱን ፡ ከመንገድ ፡ ዳር ፡ ተኝታ ፡ አገኘቻት ። በጊቷም ፡ ትሑትና ፡ ግብረ ፡ ገብነት ፡ ያላት ፡ ፍጥረት ፡ ነበረችና ፡ ከተኛችበት ፡ ብድግ ፡ ብላ ፡ እኅቴ ፡ ፍቅሬ ፡ እመት ፡ ፍየሊት ፡ ሆይ ፡



ወዴት ፡ ትሄጃለሽ ፡ ስትል ፡ ጥያቄ ፡ አቀረበችላት ። ፍየሏም ፡ አንድ ፡ ወሬ ፡ ሰምቼ ፡ ልነግርሽ ፡ ነው ፡ የመጣሁት ፡ አለቻት ።

በግም ፡ በድንጋጤ ፡ ከቶ ፡ እኔን ፡ የሚያስፈልግ ፡ ምን ፡ ጕዳይ ፡ አግኝቶሽ ፡ ይሆን ፡ እኅቴ ፤ ፍየል ፡ በግን ፡ ትክ ፡ ብላ ፡ እያየች ፡ ይኸውልሽ ፡ አንድ ፡ አዲስ ፡ ጠበል ፡ ፈልቆ ፡ ፍጥረት ፡ ሁሉ ፡ እየሄደ ፡ ይፈወሳል ፡ አሉኝ ፤ እሁንም ፡ እኔና ፡ አንቺ ፡ ሄደን ፡ ከበሽታችን ፡ ድነን ፡ እንድንመጣ ፡ ልነግርሽ ፡ ነው ፡ የመጣሁት ፡ አለቻት ።

በግም ፡ በጕዳዩ ፡ ጥቂት ፡ አሰበችበትና ፡ እኔ ፡ ለራሴ ፡ አቅመ ፡ ቢስ ፡ ነኝ ፤ አንችም ፡ ሰውነትሽ ፡ አልቋል ፤ መንገድ ፡ የምትችዪ ፡ አይመስለኝም ፤ ከዚህ ፡ በስተቀር ፡ ደግሞ ፡ እኛ ፡ እንስሳት ፡ ብዙ ፡ ጠላት ፡ ስላለብን ፡ የዱር ፡ አውሬ ፡ ያገኘን ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ አይለቀንም ፤ ስለዚህ ፡ እኔ ፡ በፍጹም ፡ እግሬን ፡ አላነሳውም ፤ ላንቺም ፡ ይህ ፡ ነገር ፡ ቢቀርብሽ ፡ መልካም ፡ ነው ፡ ስትል ፡ ሐሳቧን ፡ አቀረበችላት ። ፍየልም ፡ ምንም ፡ አትፍሪ ፡ የሚመጣውን ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ በኔ ፡ ላይ ፡ ጣይው ፡ ብላ ፡ በጊቷን ፡ ስላደፋፈረቻት ፡ ተስማሙና ፡ መንገዳቸውን ፡ ቀጠሉ ።

ጥቂት ፡ እንደ ፡ ሄዱም ፡ ከጦጣ ፡ ጋራ ፡ ተገናኙና ፡ እሷም ፡ ዛሬ ፡ ምን ፡ እግር ፡ ጣላችሁና ፡ ከዚህ ፡ መጣችሁ ፡ ስትል ፡ ጠየቀቻቸው ። ፍየልም ፡ በበግና ፡ በራሷ ፡ ስም ፡ ሆና ፡ እንዲህ ፡ ስትል ፡ መለሰች ። እግዚአብሔር ፡ የምድር ፡ አራዊት ፡ ሁሉ ፡ በድለውኛልና ፡ ነገ ፡ ሰማይን ፡ ደፍቼ ፡ ላጠፋቸው ፡ ነውና ፡ አንድ ፡ ቦታ ፡ ተሰብስበው ፡ እንዲጠብቁኝ ፡ እየዞራችሁ ፡ ለሁሉም ፡ ንገሩ ፡ ስላለን ፡ በጫካው ፡ በደኑና ፡ በሸለቆው ፡ ይኸውና ፡ እየዞርን ፡ እንለፋለን ፤ ዳሩ ፡ ግን ፡ አንቺ ፡ ወዳጃችን ፡ ስለ ፡ ሆንሽ ፡ እንድትጠፊ ፡ አንፈልግምና ፡ ቶሎ ፡ ብለሽ ፡ አምልጪ ፡ አለቻት ። ጦጣም ፡ በዚህ ፡ ነገር ፡ ደንግጣ ፡ ከዛፍ ፡ ወደ ፡ ዛፍ ፡ እየዘለለች ፡ ስትሸሽ ፡ ፍየልና ፡ በግ ፡ መንገዳቸውን ፡ ቀጠሉ ። ጥቂት ፡ እንደ ፡ ተጓዙም ፡ ዝንጀሮንና ፡ ጕሬዛን ፡ ለየብቻቸው ፡ አገኟቸው ፤ እነሱም ፡ ጦጣን ፡ ባታለሉበት ፡ አኳኋን ፡ አሞኝተዋቸው ፡ ሄዱ ። ደግሞም ፡ እንደዚሁ ፡ ለአንበሳ ፡ ለነብር ፡ ለዥብ ፡ ሰማይ ፡ የሚወድቅ ፡ መሆኑን ፡ እያስረዱ ፡ ከተጓዙ ፡ በኋላ ፤ በመጨረሻው ፡ እጠበሉ ፡ ቦታ ፡ ደረሱ ። ከጠበሉም ፡ ሰንብተው ፡

በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ይህ ፡ መልከም ፡ ሠራተኛ ፡ የነበረው ፡ ሰው ፡ ዙሪያው ፡ ገደል ፡ ስለ ፡ ሆነበት ፡ በበሮቼ ፡ አርሼ ፡ ያልሆንልኝን ፡ በሮቼን ፡ ሸጬ ፡ መልከም ፡ ሚስቴን ፡ ፈትቼ ፡ የተሻለ ፡ አገኛለሁ ፡ ስል ፡ እንደዚህ ፡ ያለ ፡ ጐስቋልና ፡ ላይ ፡ ወደቅሁ ፡ በማለት ፡ ራሱን ፡ በራሱ ፡ እየወቀሠ ፡ ተንኰለኛ ፡ መከሩን ፡ ወረተኛ ፡ ጓደኛ ፡ እያማረረ ፡ ባገር ፡ የመኖር ፡ ተስፋውን ፡ ቈርጦ ፡ ወደ ፡ አንዱ ፡ አገር ፡ ለመሰደድ ፡ አሰበ ። ጕዞውንም ፡ ቀጥሎ ፡ ከነበረበት ፡ አገር ፡ ብዙ ፡ ርቆ ፡ ከሄደ ፡ በኋላ ፡ ላንድ ፡ ሀብታም ፡ ገበሬ ፡ ተቀጥሮ ፡ በዚያ ፡ ኰጥሮ ፡ መከር ፡ የተወውን ፡ የእርሻ ፡ ተግባር ፡ ቀጥሎ ፡ ያገለግል ፡ ዠመር ። አንድ ፡ ዓመት ፡ ከሠራ ፡ በኋላ ፡ ከጌታው ፡ ምንዳውን ፡ ተቀብሎ ፡ ፈቃድ ፡ ጠይቆ ፡ ጥሎት ፡ የመጣውን ፡ አገር ፡ ለማየት ፡ ሄደ ። ብዙ ፡ መንገድም ፡ ተጕዞ ፡ ታላቅ ፡ በረሓ ፡ ወደ ፡ ሆነው ፡ ስፍራ ፡ ሲደርስ ፡ ከወደ ፡ ኋላው ፡ አንተ ፡ ሰው ፡ አትቸኵል ፡ አትቸኵል ፡ የሚል ፡ ድምፅ ፡ ስለ ፡ ሰማ ፡ በዚህ ፡ አልሆን ፡ ስፍራ ፡ ላይ ፡ የምን ፡ ድምፅ ፡ ነው ፡ የተሰማኝ ፡ በማለት ፡ ግራና ፡ ቀኝ ፡ ቢመለከት ፡ ምንም ፡ ሳያገኝ ፡ በመቅረቱ ፡ መንገዱን ፡ ቀጠለ ። ሁለተኛ ፡ ጊዜ ፡ እየደጋገመ ፡ አንተ ፡ ሰው ፡ አትቸኵል ፡ አትቸኩል ፡ እያለ ፡ አስቸገረው ። እሱም ፡ የሰው ፡ ወሬ ፡ ሰምቼ ፡ በችኰላ ፡ ሚስቴን ፡ ፈትቼ ፡ በሮቼን ፡ ሸጬ ፡ ጐስቋልና ፡ ላይ ፡ ወደቅሁ ፡ እዚህ ፡ እፊቴ ፡ ባለው ፡ በረሓ ፡ ላይ ፡ ከሚደርስብኝ ፡ አደጋ ፡ ሊከለክልልኝ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ የተላከ ፡ መልአክ ፡ የሚያሰማኝ ፡ ድምፅ ፡ ይሆናል ፡ በማለት ፡ ራሱን ፡ አጽናንቶ ፡ ወደ ፡ ፊቱም ፡ ሳይሄድ ፡ ወደ ፡ ኋላውም ፡ ሳይመለስ ፡ ከመንገዱ ፡ ዳር ፡ እጥላ ፡ ሥር ፡ ሀረፈ ። እምብዛም ፡ ሳይቈይ ፡ ወዲያው ፡ ከባድ ፡ ዝናም ፡ ስለ ፡ መጣ ፡ ለመጠለል ፡ በአሸጋጋሪ ፡ ወደ ፡ አየው ፡ ዋሻ ፡ አምርቶ ፡ ዝናሙ ፡ መጣል ፡ ሲዠምር ፡ እዚያች ፡ እዋሻ ፡ ውስጥ ፡ ሮጦ ፡ ገባ ። ጥግ ፡ ከያዘ ፡ በኋላ ፡ ወደ ፡ ውስጥ ፡ ሲመለከት ፡ ትልቅ ፡ ዘንዶ ፡ ተጠቅልሎ ፡ ተኝቶ ፡ ስላየ ፡ በድንጋጤ ፡ ባሕር ፡ ተውጦ ፡ በመንቀጥቀጥ ፡ ወይ ፡ አትቸኵል ፡ አትቸኵል ፡ ለዘንዶ ፡ ዳረገኝ ፡ እያለ ፡ ከዋሻው ፡ ለመውጣት ፡ ሲያስብ ፡ በንድ ፡ በኩል ፡ አትቸኵል ፡ ያለኝ ፡ ከዚሁ ፡ ዘንዶ ፡ ሊያድነኝ ፡ ይሆናል ፡ ቢያየኝ ፡ ኖሮ ፡ እስከሁን ፡ ዝም ፡ አይለኝም ፡ ነበር ፡ ነገር ፤ ግን ፡ ባለማየቱ ፡ ዝም ፡ ብሏል ። አሁን ፡ ስወጣ ፡ ያየኝና ፡ ተወርውሮ ፡ ይዞ ፡ ይውጠኛል ፡ በማለት ፡ እነበረበት ፡ ጥግ ፡



ተለጥፎ ፡ እንደ ፡ ቆመ ፡ በሸጋጋሪ ፡ ከዘንዶው ፡ ራስጌ ፡ አንድ ፡ መጠነኛ ፡ ገንቦ ፡ አየ ። ወይ ፡ ግሩም ፡ አትቸኵል ፡ የዘንዶ ፡ ባልደረባ ፡ አደረገኝ ፡ ደግሞስ ፡ ይህ ፡ ገንቦ ፡ ምን ፡ ይሆን ፡ እያለ ፡ የመዳን ፡ ተስፋውን ፡ ቈርጦ ፡ ወጥመድ ፡ ውስጥ ፡ እንደ ፡ ገባ ፡ ነብር ፡ ሞቱን ፡ ሲጠባበቅ ፡ ይህ ፡ የበጋ ፡ ዝናም ፡ ወዲያው ፡ አበራና ፡ ፀሐይዋ ፡ ቷ ፡ ብላ ፡ ስለ ፡ ወጣች ፡ ዘንዶው ፡ ባጠገቡ ፡ ሰው ፡ መኖሩን ፡ ሳይመለከት ፡ ለመሞቅ ፡ ተወርውሮ ፡ ከዋሻው ፡ ወጣ ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ሰውዬው ፡ ከዘንዶው ፡ አፍ ፡ ካመለጥኩ ፡ ወደ ፡ ቤቴ ፡ ልፈርጥጥ ፡ ሳይል ፡ በሸጋጋሪ ፡ ያያትን ፡ ገንቦ ፡ ተጠግቶ ፡ ተመለከተ ። እሷም ፡ ሙሉዋን ፡ ሻሽ ፡ የመሰለ ፡ ብር ፡ ይዛ ፡ ስላገኝ ፡ ተጭኖት ፡ የነበረው ፡ የድንጋጤ ፡ ሰመመን ፡ በደስታና ፡ በብርታት ፡ ተለውጦ ፡ የለበሰውን ፡ ነጠላ ፡ ዘርግቶ ፡ ከገንቦው ፡ ውስጥ ፡ ብሩን ፡ ዘርግፎ ፡ ከተሸከመ ፡ በኋላ ፡ አትቸኵል ፡ ይህን ፡ ሰጠኝ ፡ እያለ ፡ እየፈነጠዘ ፡ ወደ ፡ አገሩ ፡ መንገዱን ፡ ቀጠለ ።

እዚህ ፡ ትገባለች ፡ የማትባል ፡ ፈፋ ፡ በዝናሙ ፡ ምክንያት ፡ ሞልታ ፡ ስላገኛት ፡ ብሩን ፡ ከትከሻው ፡ አውርዶ ፡ ልብሱን ፡ አውልቆ ፡ ምርኩዙን ፡ ይዞ ፡ ለመሰለል ፡ ሲጠጋ ፡ የውሃው ፡ ኃይል ፡ የያዘውን ፡ ምርኩዝ ፡ ነጥቆ ፡ ወሰደበት ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ደፍሬ ፡ ገብቼ ፡ ቢሆን ፡ እኔንም ፡ እንደ ፡ በትሬ ፡ ይወስደኝ ፡ ነበር ። ብሎ ፡ ወደ ፡ ኋላው ፡ ተመልሶ ፡ ልብሱን ፡ ለብሶ ፡ እወንዙ ፡ ዳር ፡ ቍጭ ፡ ብሎ ፡ የውሃውን ፡ መጕደል ፡ ይጠባበቅ ፡ ዠመር ።

ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ ያ ፡ የተንኰል ፡ ምክር ፡ መክሮ ፡ ትዳሩን ፡ አስፈርሶ ፡ ሰውነቱን ፡ አጕስቍሎ ፡ እንዲሰደድ ፡ ያደረገው ፡ ተንኰለኛ ፡ ጓደኛው ፡ መልከም ፡ መልከም ፡ ልብሱን ፡ ለብሶ ፡ ዝናሩን ፡ ታጥቆ ፡ ጠመንጃውን ፡ አንግቶ ፡ ብዙ ፡ ብር ፡ በከረጢት ፡ ይዞ ፡ ከማዶ ፡ ሲመጣ ፡ ያች፣ ፈፋ ፡ ከመጠን ፡ በላይ ፡ በሆን ፡ አኳኋን ፡ ሞልታ ፡ ስላገኛት ፡ ዝናሩንና ፡ ጠመንጃውን ፡ አስቀምጦ ፡ ውሃውን ፡ ለመሰለል ፡ እንደ ፡ ገባ ፡ ያልታሰበ ፡ ድንገተኛ ፡ ደራሽ ፡ ውሃ ፡ መጥቶ ፡ ወሰደው ።

፨ ስለ ፡ ቁም ፡ ነገርና ፡ ስለ ፡ ሃይማኖት ፡ ወይም ፡ ስለ ፡ ፍቅር ፡ ማመንታት ፡ በሌለበት ፡ ቈራጥነት ፡ ሕይወትን ፡ ለሞት ፡ አሳልፎ ፡ መስጠት ፡ እጅግ ፡ ታላቅ ፡ ሞያ ፡ ነው ።

አይታወቅብኝም ፡ ብሎ ፡ ግፍ ፡ ወይም ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡ መሥራት ፡ ጊዜው ፡ ይዘግይ ፡ እንጂ ፡ በግፍ ፡ ሠሪው ፡ ላይ ፡ የበለጠ ፡ ጒዳት ፡ የሚደርስ ፡ መሆኑን ፡ መዘንጋት ፡ አይገባም ።

"ትንሽ ፡ ሥጋ ፡ እንደ ፡ መርፌ ፡ ትወጋ" ፡ የሚባለውም ፡ ስለዚህ ፡ ነው ።



ማውጫ ፡


| ማውጫ ፡ | ገጽ ፡ |
|---|---|
| መግቢያ ፡ ... ... ... ... ... ... ... | 5 |
| ስንዝሮ ፡ ... ... ... ... ... ... ... | 9 |
| ስለ ፡ አንዲት ፡ የቆቅ ፡ ልጅ ፡ በወጥመድ ፡ መያዝ ፡ ... ... | 18 |
| ስለ ፡ አንድ ፡ አባት ፡ ኑዛዜ ፡ ... ... ... ... ... | 19 |
| አንድ ፡ መነኵሴና ፡ ነብር ፡ ... ... ... ... ... | 25 |
| ስለ ፡ አንዲት ፡ ገበያተኛ ፡ ሴት ፡ ... ... ... ... | 27 |
| የሰው ፡ ገንዘብ ፡ የወሰዱና ፡ ሰው ፡ በግፍ ፡ የገደሉ ፡ ወንበዴዎች ፡ . | 30 |
| ያንድ ፡ ሽማግሌ ፡ ምርቃት ፡ ... ... ... ... ... | 33 |
| ያንድ ፡ ኸሩብ ፡ ሞት ፡ ... ... ... ... ... | 36 |
| ወታደርና ፡ ተማሪ ፡ ... ... ... ... ... ... | 38 |
| ባልና ፡ ሚስትን ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ እንዳታለላቸው ፡ ... ... | 40 |
| ያኸሩብ ፡ ልጅ ፡ ሞት ፡ ... ... ... ... ... ... | 43 |
| ሚስቱ ፡ የጐሽ ፡ ወተት ፡ አምጣ ፡ ስላለችው ፡ ሰው ፡ ... ... | 45 |
| ሁለት ፡ ሌቦች ፡ .. ... ... ... ... ... | 48 |
| አንድ ፡ በሬ ፡ ስለ ፡ ነበራቸው ፡ ቂሎች ፡ ባልና ፡ ሚስት ፡ ... ... | 50 |
| አንድ ፡ ሚስቱ ፡ የተጫወተችበት ፡ ሰው ፡ ... .. ... | 53 |
| የባልና ፡ ሚስት ፡ በተስቦ ፡ መታመም ፡ ... ... ... | 56 |
| ያንድ ፡ ድኻ ፡ ሰው ፡ ኑዛዜ ፡ ... ... ... ... ... | 58 |
| ሦስት ፡ ቂል ፡ ወንድማማቾች ፡ ... ... ... ... | 62 |
| የእሳትና ፡ ውሃ ፡ በሬ ፡ መግዛት ፡ .. ... .. ... | 63 |
| የዝንጀሮ ፡ ገደል ፡ መግባት ፡ ... ... ... .. ... | 64 |
| ድኻ ፡ ጥጃ ፡ ... .. ... ... ... ... ... | 66 |
| አንበሳና ፡ የሰው ፡ ልጅ ፡ ... ... ... ... ... | 72 |
| የዶሮ ፡ ዘመቻ ፡ .. .. ... ... ... ... ... | 74 |

